£M ኀ lW ”¦ ¼~ r L ━TŒ (M¼ L)

**Forum for Social Studies (FSS)**

*ሽመልስ አዱኛ*

# ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (1966-1983)

**ከድህነት ወደ ልማት፦ ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ**
**ተከታታይ ዕትም ቁጥር 1**
**የህትመቶች አዘጋጅ፦ ሺፈራው በቀለ**

# ድርቅንና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (1966-1983)

*ሽመልስ አዱኛ*

**የማኅበራዊ ጥናት መድረክ፣ አዲስ አበባ፣ 1997 ዓ.ም.**

©  2005 Forum for Social Studies and the Authors.

Camera Ready Copy: Prepared by Mihret Demissew

The opinions expressed in this publication are those of the authors and do not necessarily reflect the views of FSS or its Board of Advisors.

## ማውጫ

**ቀዳሚ ቃል**.........................................................................................................*i*

**መግቢያ**
*ሺፈራው በቀለ*.......................................................................................... *iii*

**ድርቅና ረሀብን ለመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች**
***ሽመልስ አዱኛ*..........................................................................................1**

# ቀዳሚ ቃል

*ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ከድህነት ወደልማት:- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ በሚለው አጠቃላይ ርዕስ ስር ጥር 20 ቀን 1997 ዓ.ም. ሂልተን ሆቴል በ12:00 ሰዓት በተደረገው ስብሰባ ላይ የቀረበ ነበር:: መግቢያውም በዕለቱ የጽሁፉን ጭብጥና የደራሲውን ማንነት ለማስተዋወቅ የተነበበ ነበር:: የስብሰባውን ዋና ዓላማም ባጭሩ ይገልጻል:: የስብሰባውን መንፈስ ለማሳየት ሲባል በዕለቱ የተነበበው እንዳለ ታትሟል:: የአቶ ሽመልስ አዱኛ ጽሁፍ ከተነበበ በኋላ ሰፊና የተሟሟቀ ውይይት ተደርጎ ነበር::*

*በዚሁ ፕሮጀክት ውስጥ ሌሎች ስምንት ጽሁፎች ይቀርቡና ስምንቱም በቅደም ተከተል ይታተማሉ:: የአቶ ሽመልስ ንግግር የመጀመሪያው መሆኑ ነው::*

*አዘጋጁ*

# መግቢያ

*ሺፈራው በቀለ*

**የተከበራችሁ እንግዶቻችን፣**

*ከድህነት ወደ ልማት:- እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ የሚለውን ዝግጅት በምንጀምርበት የመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ለመካፈል በመገኘታችሁ እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ::*

*እንደምታውቁት የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) በተለያዩ አድገት ነክ ርዕሶች ላይ ውይይት ሲያካሂድና ውጤቱንም ሲያሳትም ቆይቷል:: ለምሳሌ የድህነት ቅነሳን፣ የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ፣ የአካባቢን ሁኔታ፣ የትምህርትን ችግር፣ የምግብ ዋስትና እና የመሳሰሉትን አንገብጋቢ ጉዳዮችን በሚመለከት ጥናቶች አድርጓል፤ ተከታታይ ስብሰባዎችንም አካሂዷል:: በነዚህም ስብሰባዎች ላይ የሚመለከታቸውን መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ምሁራንንና ሌሎች ከጉዳዩ ጋር አግባብ ያላቸውን ሰዎች አሳትፏል:: ጉዳዩ በቀጥታ የሚነካቸው አርሶ-አደሮች፣ በድህነት አረንቋ ውስጥ ያሉ ወገኖችና እንደሁኔታው ሌሎች ክፍሎች እንዲካፈሉ፣ ችግራቸውን እንዲያሰሙና ሀሳባቸውን እንዲሰጡ አድርጓል:: በስብሰባዎቹም ላይ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ጥናታዊ ወረቀቶች ቀርበዋል:: ልዩ ልዩ ሀሳቦችም ተሰንዝረዋል:: ወረቀቶቹንም አሳትሟል::*

*ይህንኑ ልምድ በመቀጠል ማጥመ «ከድህነት ወደልማት:- ዕውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ» የሚል አዲስ የመወያያ ጭብጥ ነድፎ በቅደም ተከተል ውይይቶችን ማዘጋጀት ጀምሯል:: ይህ የዛሬው የመጀመሪያው ነው:: ይህም ጭብጥ በድህነትና በልማት ላይ ያተኮረ ሲሆን የሚያጠነጥነውም አሁን በአዛውንትነት ደረጃ ያለው ትውልድ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን አደረገ? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ይሆናል:: ጽሁፍ አቅራቢዎቹም በቅድመ-አብዮቷ ኢትዮጵያ በተቋም አመራር ወይም በከፍተኛ ፕሮፌሽናል ስራ ላይ ከነበሩት አንጋፋ ዜጎች መካከል የተመረጡ ናቸው:: አላማውም የቀድሞውን ልምድ፣ የቀድሞውን ድካምና ጥረት፣ የቀድሞውን እውቀት ለወጣቱ ትውልድ ለማስተላለፍ ነው::*

*ኢትዮጵያ የልማትን ጥረት ስራዬ ብላ የተያያዘችው በአፄ ኃ/ሥላሴ ዘመነ-መንግሥት ነበር:: በልዩ ልዩ መስኮች ብዙ እቅዶች ወጥተው እንቅስቃሴዎች ተካሂደው ነበር:: በነዚህ እቅዶችና እንቅስቃሴዎች የተካፈሉ ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው አንጋፋ ኢትዮጵያውያን አሉ:: ከእነዚህ ኢትዮጵያውያን መሀከል ወደውጭ ሄደው በስደት የሚኖሩት አያሌ ናቸው:: ይህንን ሀቅ ያረጋገጥነው የዚህን ውይይት ፕሮጀክት ሰርተን ዝግጅት በምናደርግበት ወቅት ነበር:: በሞት የተለዩንም ቀላል አልነበሩም:: በሀገር ውስጥ የሚኖሩትን እያፈላለግን የዚህን የንግግር*

ፕሮግራም ቀየስን፡፡ በአጠቃላይ ዘጠኝ ንግግሮች ይደረጋሉ፡፡ ዘጠኙም ይታተሙና አዲሱ ትውልድ የበፊቱ ትውልድ የነበረውን ልምድ እንዲያገኝ ይሰራጫሉ፡፡

በልማት መስክ ብዙ ጥያቄዎች ያኔም፣ አሁንም ይነሳሉ፡፡ ያኔ የሚነሱት አንዳንዶቹ ዛሬ ላይነሱ ይችላሉ፡፡ ዛሬ በዋናነት የምንጨነቅባቸው ያኔ ይሔን ያህል ትኩረት የማይሰጥባቸው ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የአካባቢ ጥበቃ፣ ድህነት ቅነሳ፣ ሥርዓተ-ፆታ፣ ሥነ-ህዝብ፣ ሚዲያና ልማት ጎልተው የመጡት ከአብዮቱ ወዲህ ባሉት ዓመታት ነበር፡፡ አሁንም በመነጋገሪያ አጀንዳችን ላይ ግንባር ቀደም ሥፍራ ይዘዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ችግሮች በየዘመኑ እየተነሱ፣ ሳይፈቱና ሳይቋጩ እየተንከባለሉ እስካሁን መጥተዋል፡፡ ለምሳሌ የገጠር ልማትና በዚሁ ውስጥ የመሬት ይዞታ ጉዳይ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው፣ የሁለተኛውና የሦስተኛወ አምስት ዓመት እቅዶች ሲነደፉም ሆነ በሥራ ላይ ሲውሉ የገጠሩ ጉዳይ ከፍ ያለ ሥፍራ ተሰጥቶት ነበር፡፡ በሌላ መልኩ ስናየው የድህነት ቅነሳም ሆነ የአካባቢ ጥበቃ፣ የምግብ ዋስትናም ሆነ የሥነ-ህዝብ ጥያቄ በቀጥታ ገንነው አይውጡ እንጂ በአዜውም ጊዜ ቢሆን ከገጠር ልማት ጉዳይ ጋር መነሳታቸው፣ የገጠር ልማት አካል ተደርገው መታየታቸው አልቀረም፡፡

ስለዚህ እነዚህ ጥያቄዎች ለምንድነው እስከዛሬ ያልተፈቱት? እነሱንስ አስመልክቶ ምን ተሰራ? ምን ታሰበ? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ይመስለናል፡፡ መንግስት በተቀየረ ቁጥር፣ ትውልድ አልፎ አዲስ ትውልድ በመጣ ቁጥር እንደ አዲስ መነሳት የለባቸውም፡፡

አዲሱ በአሮጌው ላይ፣ ወጣቱ በአንጋፋው ሥራ ላይ፣ ወደሥልጣን የመጣው ቡድን የበፊቶቹ መንግስታት በሰሩት ላይ፣ ወጣቱ ምሁር የቀድሞው ምሁራን ባሰቡት ላይ ተመስርቶ ሲሰራ ብቻ ነው ህብረተሰብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ወደፊት የሚጓዘው፡፡ አለበለዚያ ያዙሪት ጉዞ ሊሆን ይችላል፡፡ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ግን እውቀትንና ልምድን ለትውልድ ማስተላለፍ (*Intergenerational Transfer of Knowledge*) በተገቢ መልኩ የሚከናወን ባለመሆኑ ነው ማጥመ ይህንን ዝግጅት የጀመረው፡፡ በዚህም ዝግጅት የመክፈቻው ጭብጥ ይሕንኑ የአገራችንን አንገብጋቢ ጉዳይ —ድርቅ፣ ረሀብና የምግብ ዋስትናን— የሚመለከት ይሆናል፡፡ ልምዳቸውንና ትዝታቸውን የሚያካፍሉን አቶ ሽመልስ አዱኛ ናቸው፡፡

አቶ ሽመልስን ማስተዋወቅ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ ድርቅንና ረሀብን ለመከላከል በተደረጉ ጥረቶች ውስጥ ከ1966 ጀምሮ ለአያሌ አመታት በአመራር ደረጃ ሲሰሩ የነበሩ ሰው መሆናቸውን ሁላችንም የምናውቀው ይመስለኛል፡፡ ይህንንም ሰፊ ልምዳቸውን ዛሬ በአጭሩ ያካፍሉናል፡፡

አቶ ሺመልስ ጥቅምት 2 ቀን 1928 ዓ.ም. በጅጅጋ ከተማ ተወለዱ፡፡ ያ ጊዜ ለኢትዮጵያ እጅግ ቀውጢ ወቅት መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ጅጅጋ የግምባር ከተማ ነበረች፡፡ በተወለዱበት ወቅት አባታቸው አዱኛ ካሳ ግምባር ተሰልፈው ነበር፡፡ እንደተፈራውም የኢትዮጵያ ጦር ማፈግፈግ ተገደደ፤ በመጨረሻም ተረታ፡፡ በወቅቱ

አሥር አለቃ የነበሩት አዱኛ ቤተሰባቸውን ይዘው በጊዜው ብሪቲሽ ሱማሌላንድ ይባል ወደነበረው አገር ተሰደዱ:: መጀመሪያ ቦራማ በተባለው ትንሽ ከተማ ከሌሎች ስደተኞች ጋር ከተቀመጡ በኋላ በጊዜው የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ወደነበረችው ኬንያ እንግሊዞች በመርከብ ሁሉንም ወሰዷቸው:: ከሞምባሳ ወጣ ብሎ ታቬታ በምትባል ቦታ የስደተኞች መንደር መሰረቱ:: ጨቅላው ሺመልስ እዛ ለአምስት ዓመት ያህል ከተቀመጡ በኋላ ከሌሎች ስደተኞች ጋር ሆነው በ1934 ዓ.ም. ወደሀረር ተመለሱ:: ገና ከተወለዱ ጊዜ አንስቶ ብዙ መጉላላትን፣ መከራንና ውጣ ውረድን ያዩት ሺመልስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ሀረር፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አዲስ አበባ ጄኔራል ዊንጌት ተከታትለዋል:: በ1948 ዓ.ም. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (አሁን አ.አ.ዩ) ገብተው በትምህርት ዘርፍ ተከታትለው በ1952 ዓ.ም. በባችለር ዲግሪ ተመርቀዋል:: ወዲያው ወደ ህንድ ለድህረ-ምረቃ ትምህርት ተላኩ:: በ1953 በ Social Science Administration የማስተርስ ዲግሪ ይዘው ተመለሱ::

ከዛ ጊዜ ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ በተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶች በተለያዩ የሀላፊነት እርከኖች ላይ በመሆን ሰርተዋል:: በወቅቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ይባል በነበረው በአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትርፍ ጊዜም በመምህርነት ይሰሩ ነበር:: ይህ የትርፍ ጊዜ ስራቸው በወቅቱ ራዲካል የነበሩ ተማሪዎችን ሊያውቁ አስችሏቸው ነበር:: በዚህም ምክንያት የመንገድ ትራንስፖርት አስተዳደር ሀላፊ ሆነው በሚሰሩበት ጊዜ አንዳንዶቹን አብዮተኛ ወጣቶች በመሥሪያ ቤታቸው እንዲቀጠሩ አድርገው ነበር:: ለምሳሌም ያህል ዋለልኝ መኮንንና ገብሩ መርሻን መጥቀስ ይበቃል:: ይህም ወኔ የተሞላው እርምጃቸው በግራ ዘመም ምሁራን አካባቢ ትልቅ ዝናን አትርፎላቸው እንደነበር በጊዜው የነበርነው እናስታውሳለን:: እነዋለልኝ መኮንን አይሮፕላን ለመጥለፍ ያደረጉት ያልተሳካ ሙከራ አንዳንድ ጥያቄ አስነስቶባቸው እንደነበር በጊዜው ይወራ እንደነበር መጥቀስ እወዳለሁ::

አቶ ሺመልስ ወደ ብሄራዊ መድረክ የመጡት ግን ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠ/ሚር በሆኑ በጥቂት ቀን ውስጥ የእርዳታ አስተባባሪ አድርገው ሲሾሟቸው ነው:: ጊዜው የድርቁ ጉዳይ ትልቅ ብሄራዊ አጀንዳ የሆነበት ወቅት ነበር:: በዛሬው ንግግራቸው ከዛ ጊዜ ጀምሮ የነበራቸውን ሰፊ ልምድ በአጭሩም ቢሆን ያካፍሉናል::

ይህ ንግግር የሚያተኩርበት ርዕስ፡- **ድርቅ፣ ረሀብና የምግብ ዋስትና** አሁንም ቢሆን የሀገራችን ትልቅ ጉዳይ ነው:: ድርቅና ረሀብን ማሸነፍ አልቻልንም:: አገራችን ለዜጎቿ የምግብ ዋስትና መስጠት ዛሬም አልቻለችም:: በነዚህ ጉዳዮች ላይ ምርምር፣ ውይይትና ክርክር መቀጠል አለበት:: ይህም ምርምር፣ ውይይትና ክርክር ሊበለጽግ የሚችለው፤ ዘላቂ መፍትሄም የሚያመጣው ባለፈው ልምድ ላይ ሲመሰረት ብቻ ነው:: በዚህ መሰረት ነው ማጥመ ለጉዳዩ ቅድሚያ ሰጥቶ አቶ ሺመልስን የመጀመሪያው ተናጋሪ ያደረገው:: ከንግግራቸው በኋላም

በሚካሄደው ውይይት ላይ አትኩሮቱ የቀድሞው ታሪክ ላይ፣ ከቀድሞው ልምድ ምን እንማራለን የሚለው ጥያቄ ላይ ቢሆን ይሻላል።

ከንግግራቸው በኋላ የውይይት ጊዜ ይኖራል። ውይይቱ ካለቀ በኋላ ሪሴፕሽን ስላለ ወደዛ ሁላችሁም ተጋብዛችኋል፤ ውይይቱ እዛም ሊቀጥል ይችላል። በውይይቱ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን አካቶ የሚዘጋጀው ጽሁፍ በማጥመ ይታተማል። ይህም ለሚቀጥለው ስብሰባችን ይደርሳል። ውይይቱ ካለቀ በኋላ ወደሪሴፕሽን ከመሄዳችን በፊት የሚቀጥለውን ፕሮግራም እናስተዋውቃችኋለን።

አመሰግናለሁ!

# ድርቅና ረሀብን ስመቋቋም የተደረጉ እንቅስቃሴዎች

*ሽመልስ አዱኛ*

## መግቢያ

*የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ባዘጋጀው «**ከድህነት ወደ ልማት እውቀትን ለትውልድ ማስተላለፍ**» በሚል ርዕስ በተከታታይ ለአንድ ዓመት ተከቱል በሚዘልቀው የንግግሮች መድረክ አንዱ ተናጋሪ በመሆኔ ደስታ ይሰማኛ ል። አሁን ያለው አዝማሚያ «ለባቱን ሊያቅ ሊያቱን ናፈቅ» በሆነበት ጊዜ የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ለአሠርት ዓመታት ያሉንን ተሞክሮዎች ለትውልድ እንድናስተላልፍ የሚያደርገውን ጥረት ከልቤ የምደግፈውና በራስ መተማመንን ሊያበለጽግ የሚችል ይሆናል ብዬ ስለማምንበት የመድረኩን መሪዎች ከልብ ላመሰግንና አክብሮቴንና አድናቆቴን ልገልጽላቸው እወዳለሁ።*

*ዛሬ የማደርገው ንግግር የሚያተኩረው በተለይ በ1966 ዓ.ም. በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን በተመሠረተ ጊዜ አፍጥጦ የነበረውን የሕዝብ እልቂት ለመቋቋምና ከዛም በኋላ በተከታታይ የተከሰቱትን ረሀቦች ለማስቆም የተደረጉ ጥረቶች ላይ ነው።*

*ያም ሆኖ ግን ዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ከተቋቋመ ማግስት ጀምሮ በድርቅ ምክንያት የሚከሰተውን ችግር በዘላቂነት ለማስቆም ምን መደረግ አለበት፣ እንደገና ድርቅ ከተከሰተስ እንዴት መቋቋም አለብን፣ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ ሰፊ ጥናት አስጠንተናል። ጥናቱንም ለመተግበር ከዓለም ባንክ የዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት አስር ሚሊዮን ዶላር በብድር መልክ አግኝተን ነበር።*

*ስለዚህ የንግግሬ የመጀመሪያው ክፍል የሚያተኩረው የረሃብ ችግር አስገድዶት ቤት ንብረቱን ጥሎ ነፍሱን ለማዳን ዕርዳታ ፍለጋ የተሰደደውንና በየመጠለያ ጣቢያ የነበረውን ህዝብ ነፍሱን አድኖ ተመልሶ እንዲቋቋም የተደረገው ጥረት ላይ ይሆናል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ለረሀቡ ችግር የዘለቄታ መፍትሄ ይሆናሉ ተብለው የተወሰዱ እርምጃዎች ላይ ይሆናል።*

## የድርቁ ችግር መከሠት

*በ1965 ዓ.ም. በወሎና በትግራይ የተከሰተው ድርቅና ያስከተለው የሕዝብ እልቂት የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ ከዳር እስከዳር ያነቃነቀና መዘዙም የአገሪቷን የመንግሥት አስተዳደር ያናጋ፣ ከፍተኛ የሕዝብ አመጽ ያስነሳና በወቅቱ የነበረውን ሥርነቀል ለውጥ ያስከተለ ነበር።*

*በአገራችን ታሪክ የረሃብ እልቂት ለመጀመሪያ ጊዜ ተዘግቦ የሚገኘ ው በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት ሲሆን ይህም በመጽሐፈ ስንክሳር ውስጥ*

ነው:: የድርቅ ችነፈር ተደጋግሞ ሲደርስም ሕዝቦች በሚፈጽሙት ሀጢአትና በደል የተነሳ የሚከሰት የእግዚአብሔር ቁጣ ነበር ተብሎ በሰፊው ሲታመንበት ቆይቷል:: ብዙ ጊዜ የሚከተለው ረሃብ በወረርሽኝ በሽታ የታጀበ ስለነበረ ከፍተኛ ዕልቂት ያስከትል ነበር:: በአፄ ምኒልክ መንግሥት የደረሰው ታላቁ ረሀብ (1880-1883) ለዚህ አይነተኛ ምሳሌ ነው::

በድርቅ ምክንያት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ከፍተኛ የከብት እልቂትም ይከተል ስለነበር በተለይ በአርብቶ አደሩ ሕዝብ ላይ በቶሎ የማይቀረፍ ከፍተኛ የችግር ጠባሳ ይተው ነበር:: በከብት እልቂቱ ምክንያት አርሶ አደሩ ማረሻ በሬውን ሲያጣ አርብቶ አደሩ ደግሞ ከብቱን ሲያጣ የኑሮው ዋልታ ስለሚናጋ ለዓመታት የሰው እጅ ለማየት ይገደድ ነበር::

በኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ ከፍተኛ የአምበጣ መንጋና የተምች ወረርሽኝ የተዘራውን ሰብል እስከ ስሩ ስለሚላጨው፣ ዛፍና ቁጥቋጦውንም መለመላውን ስለሚያስቀረው ከባድ የረሃብ ችነፈርና የከብት እልቂት ይከተል ነበር:: በ1965 ዓመተ ምህረትና በተከተሉት ዓመታትም ከባድ የአንበጣ፣ የተምችና የፌንጣ ወረርሽኝ በስፋት ተከስቶ ነበር:: ምንም እንኳን የምሥራቅ አፍሪቃ የአንበጣ መከላከያ ድርጅት ቢኖርም እንደልቡ ተዘዋውሮ መድኃኒቱን ለመርጨት በአንድ በኩል የአምበጣ መፈልፈያ በሆኑት አካባቢዎች:- ማለትም በምስራቅ በኦጋዴን፣ በሰሜን በኤርትራ — ይካሄዱ የነበሩት የእርስ በርስ ጦርነቶች እንቅፋት ሆነውበት ነበር፤ በሌላ በኩል አይሮፕላኖቹን ለመጠገንና ከአየር የሚረጨውን ፀረ አንበጣና ተምች መድኃኒት ለመግዛት

*የሚያስፈልገውን ወጭ መሸፈን ስላልቻለ ድርጅቱ የታለመለትን ተግባር መፈጸም አልቻለም ነበር።  አባል አገሮችም የመዋጮ ድርሻቸውን ስለማይከፍሉ ችግሩን አባብሶት ነበር።*

*እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነበር ተማሪው ለዘመናት «ደሃው ይናገራል» የሚለውና የመሳሰሉትን ግጥሞች በመፃፍ የሕዝብን ችግር በመግለጽ ለለውጥና ለልማት ሲያደርግ የነበረው ትግል፣ የመሬት ላራሹ ሰልፍና ልዩ ልዩ የዲሞክራሲና የመብት ጥያቄዎችን በሕዝባዊ ሰልፍ ሲገልጽና በዩኒቨርሲቲ ሲያደርግ የነበረው የትምህርት ማቆም አድማና ሲከፍል የነበረው መስዋዕትነት እውን ሊሆን የተቃረበው። ያን ጊዜ ነበር የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ብቅ ብሎ "ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" እያለ የለውጥ አጋፋሪ ሆኖ ግምባር ቀደም ሚና ለመጫወት የተነሳው።*

በዚህ ጊዜ ነበር ጆናታን ድምብልቢ የሚባለው ጋዜጠኛ የተደበቀው ረሃብ (*"The Hidden Hunger"*) በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን ፊልም በቴምስ ቴሌቭዥን ላይ በማቅረብ ይፋ ያደረገው። በዚህ ፊልሙ አሰቃቂውን የወሎን የረሃብ ዕልቂት ከማሳየቱም በላይ ፊልሙን ሲጀምር *«በምዕራብ አፍሪቃ ከብቶች ሲያልቁ በኢትዮጵያ ግን ሰዎች እያለቁ ነው።»* በማለት የዓለምን ሕዝብ በየቤቱ ገብቶ ልቡን ሰበረው።

1. **የዕማማኮ መቋቋም**

*የጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተ ወልድ ካቢኔ ሥራ ለቆ ልጅ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ምኒስትር ሆነው ሲሾሙ ከተደረገው ሹመት መሐል የደጃዝማች ከበደ ተሰማ የግቢ ምኒስትርነትና የኔ የዕርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነርነት ከመጀመሪያዎቹ መሐል ነበር። ይህም በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ነበር።*

*እኔም በሃላፊነት እንድመራው የተቋቋመው የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የተወለደው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ባለች ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር። በትዕዛዝ ቁጥር 93/1966 ነበር ኮሚሽኑ በሕግ የተቋቋመው። ሥራውም ሲጀመር ቀደም ሲል በእህል እጥረት ኮሚቴ ውስጥ ይሰሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያንና ከዓለም የምግብ ፕሮግራም አለን ጆንስ፣ ከአትላንታ የበሽታ ቁጥጥር* (CDC) *አንድ ሐኪም፣ከዩኒሴፍ አንድ ስዊድናዊት ተባባሪ ባለሙያ በድምሩ ሰባት ሰዎች ሆነን ነበር ሥራውን የጀመርነው። ቀደም ሲል መጥተው በወሎ ውስጥ የሚሠሩ ምግባረ ሠናይ ድርጅቶች፣ ከየመሥሪያ ቤቱ የተውጣጡ ሠራተኞችና የክፍለ ሃገሩ እንደራሴና የአውራጃ አስተዳዳሪዎች በየወረዳውና መንገድ ዳር ባሉ ከተሞች ውስጥ መጠለያ ሰርተው እርዳታ በመስጠት ላይ ነበሩ። እነሱንም ማስተባበር ነበረብን።*

*በ1966 እና 1967 ዓ.ም. ድርቁ በተከሰተበት ወቅት በተለይ በወሎ፣ በትግራይና በሰሜን ሸዋ ህዝቡ እየተሰደደ መንገድ ዳር ሲወጣ የመጀመሪያው ጥረት የተደረገው በአስቸኳይ ህይወት አድን የሆነ*

ዕርዳታ መስጠት ነበር:: እ.ኤ.አ. በኤፕሪል 13/1973 እህል ወደ ውጭ እንዳይወጣ ታገደ:: ለጅቡቲ ግን በፈቃድ ይላክ ነበር:: በዚያን ወቅት በወሎ መጠለያ የነበረው ህዝብ ብዛት 280,000 እንደነበረ ከወሎ ጠቅላይ ግዛት የተላከው ሪፖርት ሲያመለክት መንግስት ለዕርዳታ ሰጪዎች ያቀረበው የእህል ጥያቄ 60,000 ቶን ለ200,000 ሰዎች ብቻ የሚበቃ ነበር:: በዚህ ጊዜ በወሎ 100,000 ሰዎች እንደሞቱ በወቅቱ የነበሩ መያዶች ሪፖርት ያመለክታል::

ሥራችንን ስንጀምር ያተኮርነው ነፍስ አድን ተልእኮ ላይ ስለነበር ሌትና ቀን መረባረብ ነበረብን:: ከህዝቦች፣ ከመንግስትና ከዓለም አቀፍ መያዶች ሰፊ እርዳታዎች አግኝተናል:: እነዚህን ሁሉ ሀይሎች በማስተባበር ባደረግነው ጥረት በጀመርን በጥቂት ወራት ውስጥ የሰውን ማለቅ ለማስቆም ችለን ነበር:: በዓመቱ ማለት በ1967 ዓ.ም. መሀከል ላይ ድርቁ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ውሎ ነበር:: ይሁንና ዓመቱ ገና ሳያልቅ ድርቁ በሌሎች አካባቢዎች እንደገና ስለፈነዳ ችግራችንን አወሳሰቦብን ነበር::

ዕማማኮ እንደተቋቋመ 2,500,000 ብር ዕርዳታ ጠይቆ ነበር ስራውን የጀመረው:: በግዜው መረጃ በሚገባ መሰብሰብ አስቸጋሪ ስለነበረ የደረስንበት ግምት 400,000 ህዝብ የተራበ መሆኑንና በ1967 ደግሞ በአምስት አውራጃዎች የተራበው ህዝብ 524,000 እንደደረሰ ይገመት ነበር:: በ1967 ዓ.ም. ድርቁ በ11 ጠቅላይ ግዛቶች ተስፋፍቶ በነበረበት ወቅት አስተማማኝ መረጃ ሰብስበን በሚገባ ያቀረብነው ሪፖርት የሚከተለው ነው::

| ክፍለ ሀገር | የገጠሩና አርብቶ አደሩ ህዝብ | ዕርዳታ ፈላጊ ህዝብ | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ኤርትራ | 1,779,400 | 1,002,000 | 56.3% |
| ትግራይ | 1,993,600 | 963,000 | 48.5% |
| ወሎ | 2,456,400 | 956,000 | 38.7% |
| ጎንደር | 1,914,200 | 90,000 | 4.7% |
| ሸዋ | 4,584,800 | 70,000 | 1.5% |
| ሐረርጌ | 2,888,600 | 1,001,500 | 34.7% |
| ባሌ | 836,400 | 515,000 | 70.2% |
| ሲዳሞ | 2,560,600 | 270,000 | 10.5% |
| ጋሞ ጎፋ | 939,000 | 227,500 | 24.1% |
| ድምር | 1,995,300 | 5,161,280 | 25.9% |

እነዚህ አሀዞች በሚገባ እንደሚያሳዩት፣ የነፍስ አድን ስራው በቀላሉ የሚቆም አለመሆኑን ነበር:: ስለዚህ ዕርዳታ የማደሉ ዘመቻ በስፋት ቀጠለ:: አንዱን የድርቅ ዘመን ስንቋቋም ሌላ ድርቅ፣ ቀጥሎም ረሀብ

ሌላ ቦታ እየተከሰተ ለረጅም ጊዜ ሲያስቸግረን ኖረ፡፡ ይሁንና በዕርዳታ ሥራ ብቻ ተጠምደን የረጅም ጊዜ ራዕይ ከመንደፍ አልታቀብንም፡፡

እኔ በተሾምኩበት ወቅትና ከዛም በኋላ አገራችን በታላቅ የአብዮት ነውጥ ውስጥ ስለነበረች መንግስት በብዙ አቅጣጫ ተወጥሮ ነበር፡፡ ይሁንና የመንግስት ከፍተኛ መሪዎች ለረሀቡ ትልቅ ትኩረት ስለሰጡት እኔ የምሰራውን ሥራ ይከታተሉና ያነቃቁኝ ነበር፡፡ በተሾምኩበት ዕለት አፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ ሰጥተው ባያነጋግሩኝም ከጥቂት ቀን በኋላ አስጠርተውኝ በስራው እንድገፋበት ከፍተኛ የማነቃቃት ንግግር አድርገውልኝ ነበር፡፡ ከዛ በኋላም በየጊዜው ማታ ማታ እቤቴ እየደወሉ እንቅስቃሴያችን እምን እንደደረሰና ምን ችግር እንዳጋጠመን ይጠይቁኝ ነበር፡፡ ምንም እንኳ ጊዜያቸው እጅግ የተጣበበ ቢሆንም ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸውም በሥራ ሰዓት በተቻለ መጠን በፈለግሁበት ሰዓት ላገኛቸው እንድችል ለረዳታቸው መመሪያ ሰጥተው ነበር፡፡ ማታ ማታም አስቸኳይ ጉዳይ ኖሮኝ ከፈለግሁዋቸው አልጋቸው አጠገብ ያለውን ቴሌፎን ቁጥር ሰጥተውኝ፣ በፈለግሁበት ሰዓት እንድደውል ፈቅደውልኝ ነበር፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የሥራዬን መቀላጠፍ ረድተው ነበር፡፡

ደርግ ስልጣን ላይ በወጣበት ጊዜም ሌ/ጀ አማን አንዶምም ሆኑ ብ/ጄ ተፈሪ ባንቲ ለስራ ከፈለግኋቸው በረዳታቸው በሻምበል መለሰ ማሩ በኩል እያገኘኋቸው ውሳኔ በማግኘት እሰራ ነበር፡፡ ኮ/ል መንግስቱ ኃይለማርያምም ስለስራዬ በመረዳትና በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጡኝ ነበር፡፡

ከከፍተኛ መሪዎቻችንም ሆነ ከህዝቡ፣ ከዓለም ዓቀፍ ተቋማትም ሆነ ከመያዶች ትልቅ ድጋፍ ቢኖረንም ችግሩ እጅግ ሰፊ ስለነበረ በቀላሉ የሚቀረፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ እንዲያውም የመደጋገምና ባልተጠበቁ አካባቢዎች የመፈንዳት ባህርይም ያሳይ ነበር፡፡ ስለዚህ ችግሩን በቋሚነት ለመፍታት ምን መደረግ አለበት የሚለው ጥያቄ ገና ከመጀመሪያው አሳሳቢ ሆኖ አግኝተነው ነበር፡፡

## ፪. የኮሚሽኑ የትኩረት አቅጣጫ

የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኰሚሽን ሲቋቋም ቅድሚያ ተግባሩ አድርጐ የተነሳው ወገኖቻችንን ከሞት ማዳን ቢሆንም በግዜው በድርቅ መጎዳታቸው በይፋ ይነገር በነበረው በወሎና በትግራይ ጠቅላይ ግዛቶች ውስጥ የመልሶ ማቋቋም ሥራ እንዲከናወን ከዓለም ባንክ ጋር በመነጋገር በተገኘ ድጋፍ *ወሎንና ትግራይን ከድርቅ መልሶ ለማቋቋም ጥናትና የኘሮጀክት ዝግጅት በጥቅምት 1967 - «Drought Rehabilitation in Wollo and Tigray - Report of a Survey and Project Preparation Mission October - November 1974»* የተባለውን ጥናት በጥር 1967 (January 1975) እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

በዚህ ሪፖርት ላይ እንደሚታየው የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ትኩረቱ የእለት ዕርዳታ መስጠት ብቻ ሳይሆን

ለረሃቡ ምክንያት የሆኑ ሁኔታዎችን ማወቅና ሁኔታውን ያባባሱ ምክንያቶችን በመመርመር የመፍትሄ ሃሳቦችን ማቅረብ ነበረ፡፡ በዚህም መሠረት የሕዝብ እልቂትን ለማቆም በድርቁ ምክንያት ቀዬውን ለቆ በየመጠለያው ፈሶ የነበረው ሕዝብ ወደ ቤቱ እንዲመለስ፣ አመቺ የሆነውን አካባቢ ማረስና መዝራት እንዲችልና በልማት እንዲሠማራ በሬ፣ ዘርና ማብሰያ ማቅረብና ሰብሉ እስኪደርስለት ድረስ ደግሞ የሚበላው እህል መስጠትና ራሱን እንዲችል የሚያግዙ ፕሮጀክቶችና ለወደፊት ሊመሩ የታቀዱ የረጅም ጊዜ ፕሮጀክቶችን አሰባስቦ በባለቤት መሥሪያ ቤቶቻቸው በኩል እንዲሠሩ ብድርና እርዳታ እንዲገኝላቸው ማገዝ ነበር፡፡

**የረሀቡ ዋና ዋና ምክንያቶች**

1. ለዘመናት ታይቶ የማይታወቅ ሀይለኛ ድርቅ መከሰት፤

2. ግዴለሽ የመሬት አጠቃቀም ያስከተለው የመሬት መበላትና መሸርሸር፣ አፈሩ ለእርሻ ምርታማ አለመሆኑ፤

3. የሕዝብ ቁጥር ማደግና ለየቤተሰቡ የሚደርሰው የመሬት መጠን እጅግ ማነሱና ከዚህም አነስተኛ ይዞታ የሚገኘው ሰብል አናሳ መሆኑ፣ የከብትም ቁጥር መጨመሩና የአካባቢው ግጦሽ መመናመኑ የአርብቶ አደሩን ኑሮ አስቸጋሪ ማድረጉ፤
4. የማያስተማምንና ኢፍትሃዊ የመሬት ይዞታ ሥርአት በምርታማነት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ናቸው፡፡

**ችግሩን ያባባሱት ታሳቢዎች**

- የመገናኛ አለመመቻቸት:- 1ኛ/ ምንም አይነት መረጃ የረሃቡ አደጋ ከደረሰበት አካባቢ ወደ ክፍለ ሃገሩ ዋና ከተማ አለመድረስ፣ 2ኛ/ ችግሩ ከታወቀ በኂላም መንገድ ባለመኖሩ ዕርዳታውን ለማድረስ አለመመቻቸቱና ከፍተኛ ዋጋ መጠየቁ፤

- የምግብ ዋስትና ክምችት ዝግጁነት በአገር ውስጥ አለመኖር፣ እህል ከውጪ እስኪመጣ ለመጠበቅ መገደድና በዚህም ምክንያት ረሃብ፣ በሽታና ሞት መከተሉ፤

- ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት መንግሥት አፋጣኝ እርምጃ ወስዶ ዕርዳታ በመጠየቅ ለተቸገረው ወገን አለመድረስ፤

- አውድ አመትና አመትባል በመብዛቱ ዘወትር ስለማይሰራ ባሉት የሥራ ቀናት ቶሎ ቶሎ ለማረስ ተጨማሪ በሬዎች ማስፈለጋቸው፤

- ሌሎችም ሁኔታውን ያባባሱ ምክንያቶች ከአሠራር ዘገምተኝነት ጀምሮ በርካታ ስለሆኑ በአስር አመት ውስጥ ሊወገዱ እንደማይችሉ ጥናቱ ያመለክታል:: ያ ችግር ዛሬ ከሰላሳ ዓመት በኋላም እንዳፈጠጠ ነው::

**የመፍትሄ እርምጃዎች**

የመፍትሄ ሀሳቦቹ ዘላቂነት እንዲኖራቸው ወቅታዊ መፍትሄ የሚሰጡ ፕሮጀክቶችን አቅዶ መፈጸም ብቻ ሳይሆን የችግሩ ስር መሠረቱ በልማት ኋላ ቀርነት እንደመሆኑ መጠን አጠቃላይ አገር አቀፍ ፖሊሲ ተነድፎ በመገናኛ፣ በውሃ ልማትና በመሬት አጠቃቀም አመርቂ እርምጃ በመውሰድ ፍትሃዊ የመሬት ይዞታ ለውጥ በማድረግ (እስከዛሬም ያልተፈታና አወዛጋቢ ጉዳይ) እና መልካም አስተዳደር በማቆም ችግሩን ለመቅረፍ ይቻላል::

1. የተደጋጋሚ የድርቅ ችግር በሰላሳ፣ በአሥርና በአምስት አመት ሲከሰት የቆየ ከአሲድ ዝናብ፣ ከመኪናዎች የሚወጣ ጭስ፣ ከምንጨፈጭፈው ደንና ከኦዞን ሽፋን መሸንቆር ጋር ተያይዞ ከሚመጣው በአሁኑ ጊዜ የጥናትና ምርምር ትኩረት የሆነው የዓለም እየሞቀች መሄድ (global warming) እስካለ ድረስ ልናቆመው አንችልም:: ቢሆንም የድርቅን መከሰት መተንበይ እንድንችል ከዘመናዊ የአየር ሁኔታ ትንበያ አቅም ካላቸው አገሮችና ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ልንዘጋጅ ይገባናል:: በአሁኑ ጊዜ በየአሥርና አምስት ዓመት ይደርስ የነበረው ችግር አሁን በእየሁለት አመቱና አንዳንድ አካባቢም በየአመቱ እንደሚደርስና በቀድሞው መንግሥት እስከ ስምንት ሚሊዮን የነበረው የተረጂ ቁጥር በ1995 እና 1996 እስከ 17 ሚሊዮን ሊደርስ እንደሚችል በአገሪቷ ከፍተኛ ባለሥልጣንና በቢ.ቢ.ሲ.ና በሲ.ኤን.ኤን ሲገለጥ ተደምጧል::

2. የመሬት አጠቃቀምን ችግር ለመፍታትም በአፈር ጥበቃ፣ በደን ተከላ፣ በተሻለ አስተራረስ ዘዴ ምርታማነትን በማሳደግ፣ በተሻለ ዘርና በማዳበሪያ በመጠቀም ምርትን እስከ አምስት እጅ ለማሳደግ ስለሚቻል ተግባራዊ ማድረግ:: ከተወሰነ መለኪያ በላይ ተዳፋትነት ያላቸውን አካባቢዎች ለዛፍ እንጂ ለእርሻ ሰብል አለማዋል:: ለም አካባቢዎች ላይ ትኩረት በመስጠት የተበላ አካባቢ ላይ ገንዘብና ጉልበት ከማፍሰስ ተቆጥቦ የሰብል ምርትን በማሳደግ ትርፍ አምራች አካባቢዎችን የምግብ ዋስትና ዋልታ ማድረግ::

3. ሀ/ የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄድ በግልጽ የሚታይ ሲሆን በ1946 ዓ.ም. 7 ሚሊዮን የነበረው በ1970 ዓ.ም ወደ 22 ሚሊዮን ከፍ ብሎ በ1997 ዓ.ም. 74 ሚሊዮን ደርሷል:: ለዚህም መፍትሄው የቤተሰብ ምጣኔ ማድረግና የተጠናና አዋጪነቱ የተረጋገጠ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የሠፈራ ፕሮግራም ማካሔድ ነው:: ሠፈራ ውድ

ስለሆነ (ወጪው በ1966 ዓ.ም. ግምት እንኳን በቤተሰብ አንድ ሺህ የአሜሪካን ብር ስለሆነ) በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው:: የሕዝብ ማስፈሩ ፕሮግራም ለተወሰነ ጊዜ ሊያገለግል ይችል እንደሆነ ነው እንጂ የሕዝብ ቁጥር ከ2.9% እስከ 3% እያደገ በሚሄድበት አገር ዘላቂ መፍትሄ ሊሆን አይችልም:: የአገሪቷን የቆዳ ስፋት በማየት በቂና አስተማማኝ የዝናብ መጠን በሌለበት ቦታ ሕዝብን ማስፈር የአካባቢውን ደንና ቁጥቋጦ አበላሽቶ አፈሩንም በአጭር ጊዜ ከለምነት ወደ በረሃማነት ስለሚለውጥ ሕዝቡን ለቀጣይ ችግርና ረሃብ መዳረግ ይሆናል::

ለ/ ለዘለቄታው ከአገሪቷና ከቤተሰቡ የኢኮኖሚ አቅም ጋር የሚጣጣም የቤተሰብ መጠን መኖር እንዳለበት ሕዝብን ማስተማርና ለሚፈልጉትም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን በበቂ መጠንና በአመቺ ሥፍራ ማቅረብ አስፈላጊ ነው:: የቤተሰብ ምጣኔን በአስተማማኝነት ለማቅረብ የገጠር ልማት ፕሮግራሞችንና የጤና አገልግሎት ፕሮግራምን አቅርቦት አንድ ጋር መንደፍ ያስፈልጋል::

የሕዝብን ቁጥር መቆጣጠር ጠቀሜታን ከትምህርት ቤት ጀምሮ ማስተማር ያስፈልጋል:: የኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከሚሰጡት ትምህርት ጋር ስለገጠር ልማት ፕሮግራም፣ ስለ እርሻ፣ ስለ ጤና፣ ስለ አካባቢ ጥበቃ እንዲያስተምሩ ተደርጎ የአገሪቷ መሬትና ኤኮኖሚ ሊሸከም የሚችለውን የሕዝብ ቁጥር ያህል ብቻ እንዲሆን መደረግ አለበት:: ያም ሆኖ የአገሪቷን አጠቃላይ ልማት በአፋጣኝ በመከወን የኢንዱስትሪ፣ የማዕድንና የሀይል ማመንጫን ክፍል ማራመድና ማጎልበት ያስፈልጋል:: ቀላል ለማይባል ህዝብ ሥራ ሰጥቶ የሚገኘው «ኢንፎርማል ሴክተር» ታግዞ ወደ መለስተኛ ኢንዱስትሪ፣ መለስተኛው ደግሞ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ የሚያድጉበትን መንገድ በሥልጠና፣ በፍትሃዊ አስተዳደር፣ በብድርና በቴክኒክ ድጋፍ ማጎልበት ያስፈልጋል::

### ፫. የመሬት ይዞታ መሻሻል

ከመነሻው ባለቤትነትን የማያረጋግጥና ኢፍትሃዊ የሆነ የመሬት ይዞታ ሥርአት መስተካከል አለበት:: በተጨማሪ የተሻሉ የእርሻ ዘዴዎች እውቀትና አስፈላጊ የእርሻ ግብአቶች ለምርታማነት በጣም፣ እጅግ በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ የሚቀርቡበት መንገድ መፈለግ አለበት:: ለዚህ ነው የጭሰኛውም ሆነ ትልቁ የሀብታም ይዞታ እኩል ተጎሳቁለው ለምነታቸው የተጠበቀና የተሻሻሉት ከሕዝብ ብዛት የተነሳ መሬት በየጊዜው እየተሸነሸነ ከተበጣጠሰ የባለቤትነት መረጋገጥ ብቻውን መፍትሄ የማይሆነው:: የርስት አገር ስሪት ባላቸው አካባቢዎች እንኳን የመሬት ይዞታ በመከፋፈል አመርቂ ሰብል እንዳይገኝ የበሬ ግምባር የሚያህል ይዞታ እንቅፋት የሚሆነው ገበሬው ይዞታ ሞፈር ዘመት ሄዶ የማያርስ ከሆነ ተገቢውን የቅርብ እንክብካቤ ለሰብሉ ሰጥቶ ምርታማነቱ አጥጋቢ እንዲሆን ማድረግ አዳጋች ነው::

*በወቅቱ የነበረው የመሬት ይዞታ፣ የርስት አገር፣ የጭሰኛና የገባር መሬትም ቢሆን፣ ተለውጦ ፍትሃዊና አስተማማኝ የመሬት ባለቤትነት ያረጋገጠ ይዞታ ቢመቻችም ምርታማነቱ የሚረጋገጠው፣*

1. *ተገቢ የሆነ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ምርታማነት ላይ ያተኰረ የልማት ቅድመ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ብቻ ሲሆን ዋናው የአጭር ጊዜ ቅድመ ሁኔታ የአፈር ጥበቃ ሲኖር ነው::*
2. *እያንዳንዱ ገበሬ ሊያገኘው የሚችል የሠለጠነና ቋሚ የኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ፀረ ተባይ መድኃኒት እና ብድር አቅርቦት አስተማማኝ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው::*

**የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት:-** *ነሐሴ 29/66 የወጣው የሕግ ትዕዛዝ 93/66 የአደጋ መከላከልንና ዝግጁነትን ጉዳይ ሲደነግግ ሠፈራንም እንደ አንድ ተግባር ጨምሮታል::*

- *የአደጋ ትርጉምን ያስቀምጣል፣*
- *የዕለት ደራሽንና መልሶ ማቋቋምንም በሚመለከት ደንግጓል::*

*የ1966 ዓ.ም. ድርቅ ያስከተለው የረሃብ ዕልቂት ሲከሰት የተደራጀ የአደጋ መከላከልና መልሶ የማቋቋም ዝግጁነት አልነበረም:: ቀደም ሲል የተጠቀሰው አጥኚ ቡድን ባሳሰበው መሠረት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ትምበያ፣ መገናኛ መንገድ፣ ማጓጓዣ (ትራንስፖርት)፣ እህል ማከማቻ መጋዘኖችና ለአደጋ ጊዜ የሚውል መጠባበቂያ የእህል ክምችት በቅድሚያ ሊዘጋጁ የሚገባቸው ድርጅቶች ነበሩ::*

**መገናኛ**

*በአገራችን በተለይ የገጠር መንገዶች ባለመስፋፋታቸው እርዳታ ማድረሱ በጣም አስቸጋሪ ነበር:: ስለዚህ የመጀመሪያው አፍላ ረሃብ በወሎና በትግራይ ሲከሰት በወሎ የነበረው የገጠር መንገድ 1,000 ኪሎ ሜትር ብቻ ሲሆን በትግራይ ደግሞ 3,000 ኪሎ ሜትር ብቻ ነበር:: ከዚህም የተነሳ የእርዳታ እህል ለማዳረስ ትግራይ የተሻለ አመቺነት ነበረው:: ለአስቸኳይ መፍትሄ በተደረገው ለገጠር መንገድ ሥራ ጥናት የተቋቋመው ግብረ-ሃይል በሦስት አመት ውስጥ በትግራይ ተጨማሪ 400 ኪሎ ሜትር በወሎ ደግሞ 600 ኪ.ሜትር መንገድ ተሰራ:: በመንገድ ችግር ምክንያት በምዕራብ ጀርመን አየር ኃይል እህል ከሰማይ ይጣልላቸው የነበሩት ካበ ሃራና አረባቲ ቦራ በጀርመን እርዳታ፣ የቆቦ ላሊበላ መንገድ በቴር ደዞም ኔዘርላንድስ ተሠራ::*

*ይኼ ሠፊ አገር በእየጠቅላይ ግዛቱ የሚደርሰውን ችግር ለማወቅና የሚያስፈልገውን የዕርዳታ አይነትና መጠን አውቆ ለወገን ለመድረስ መረጃውን ማስተላለፊያ ስልክም ሆነ ሬዲዮ ባለመኖሩ ከባድ ችግር ነበር:: ስለዚህ የሬዲዮ መገናኛ ማቋቋሙ አንገብጋቢ ጉዳይ ነበር::*

የሬዲዮ መገናኛዎች ማቋቋሙ ሥራ ተፋጥኖ በ1977 ዓ.ም. 58 ቋሚ እና 26 መኪና ላይ የተጠመዱ የሬዲዮ መገናኛዎች ስለተተከሉ የእርዳታ ሥራውን ለማከናወን ጥሩ እገዛ አድርጓል:: ከዚህም የተነሳ ዕማማኮ ከፌርፌር (ደቡብ) እስከ ቃሮራ (ኤርትራ) በሬዲዮ መገናኘት ይችል ነበር::

**የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች (ትራንስፖርት)**

በመቶ ሺ የሚቆጠረውን የእህል ኩንታል ለማጓጓዝ ትራንስፖርት ትልቁ መሣሪያ መሆኑ ግልጽ ነው:: ሌላው የኢኮኖሚ ክፍል በተለይም የወጪና ገቢ ንግድ እንቅስቃሴ ከሚያስፈልገው በተጨማሪ የእርዳታ እህሉን ከዋና መንገዶች ተገንጥለው ወደ ውስጥ በሚገቡ በሚገባ ያልተሰሩ በተለምዶ «ፒስታ» በሚባሉ መንገዶች ላይ እርዳታ የሚያደርስ የተሽከርካሪ አቅም አልነበረም:: በምፅዋ፣ በአሰብና በጅቡቲ ተከማችቶ የነበረው እህል ቶሎ ቶሎ ሊጓጓዝ ባለመቻሉ በወቅቱ የነበሩ ጋዜጠኞች ሁለት ክፍል ውስጥ የነበሩ ሰባት የዕማማኮ ሠራተኞች ላይ ከባድ ወቀሳ ይሰነዝሩ ነበር:: በከተማ ፖስታ ለማደልና አንዳንድ ስብሰባዎች ለመሄድ እንኳ የኰሚሽነሩ የግል መኪና ብቻ ነበር ያለው:: በዚህ ጊዜ የጦር ሠራዊቱ መኪኖች የእርዳታ እህል እንዲያደርሱ ቢመደቡም በጎማና በመለዋወጫ ችግር አመርቂ እገዛ ለማድረግ ስላልቻሉ የአሜሪካ መንግሥት በትልልቅ የጭነት አይሮፕላኖች የመኪና ጐማዎችንና የተወሰኑ መለዋወጫ እቃዎችን በአፋጣኝ ስለላከ የሠራዊቱን መኪኖች መጠቀም ተችሏል::

የእንግሊዝ የውጪ ኤኮኖሚ ትብብር ምኒስትር የነበሩት ጁዲት ሃርት (Judith Hairt) ችግሩን ሳስረዳቸው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እያንዳንዳቸው 50 ኩንታል የሚጭኑ ሃምሳ ቤድፎርድ መኪኖች በአይሮፕላን ተጭነው እንዲደርሱን አድርገዋል::

እያደርም የምዕራብ ጀርመንና የኢጣሊያን መንግሥታትም እገዛ አድርገዋል:: UNDP እና WFP ከዕማማኰ ጋር በመሆን የትራንስፖርትና የቴክኒክ ድጋፍ ፕሮጀክት ሰርተው ለዕርዳታ ትራንስፖርት ተቋምና (Relief Transport) በተለይም ለስደተኞችና በአገር ውስጥ ለተፈናቀሉ ሰዎች ዕርዳታ የሚያቀርብ ተቋም (Transport Organisation for Relief) ፈጠሩ:: እነዚህ ተቋማት በ1984 ዓ.ም. ላይ 1,547 ባለተሳቢ ተሽከርካሪዎችና ሥራውን ለማካሄድና መኪናዎቹን ለማሽከርከር 1,598 ቋሚና የኰንትራት ሠራተኞች ነበራቸው::

በትራንስፖርት በኩል ጥቂት አውሮፕላኖችም ድርጅቱ ነበረው:: ይህን ለማቋቋም የኢትዮጵያ አየር ሃይልን በማቋቋም ብዙ አስተዋጽዎ የነበራቸውና በመጨረሻ እኔን ለሥራ ይዘውኝ ሄደው በሶማሌ ወራሪዎች የተገደሉት ካርል ጉስታፍ ፎን ሮዘን የንትንቮርግን ጋዜጣ ኅትምበርግ ፖስት ባደረገላቸው ድጋፍ አንድ ዲሲ ስሪ እና ሦስት Sab MI 15 የሚባሉ አነስተኛ አይሮፕላኖች ለድርጅቱ እንዲገኝ አድርገዋል::

ውስታቸው ለዘላለም የሚዘነጋ አይደለም:: በአይሮፕላን ዕርዳታ በማድረስ ላይ እያሉ ከተሰውት መሐል የኢትዮጵያ አየር ኃይል ባልደረባ መቶ አለቃ ኃይሌ እና Christianson የሚባል የስዊድን ተወላጅ ይገኙበታል:: የካርል ጉስታፍ ፎን ሮዘን ልጅ Eric Von Rosenም ከባድ አደጋ ደርሶበት ሊተርፍ ችሏል:: እነዚህ ሦስቱም አደጋዎች የደረሱት በጋሞ ጎፋ ጠቅላይ ግዛት ነው::

## የመጋዘንና የእህል ማከማቻ ቤቶች

ችግሩ እንደደረሰ ችግር ያለበት አካባቢ ዕርዳታ ለማስቀመጥ የተዘጋጀ መጋዘን ካለመኖሩ የተነሳ እህል የሚቀመጠው፣ ትምህርት ቤት አካባቢ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አጠገብ፣ ጊዜያዊ ጥርጊያ ማረፊያ አጠገብ ሲሆን እዚያው ማረፊያው ዳር በኘላስቲክ እየተሸፈነ ነበር:: እህሉን ዝናብ እንዳያበላሸው መሸፈኛ የሚሆን ፕላስቲክ ከውጪ መምጣት ነበረበት:: በዚህ በኩል የምዕራብ ጀርመን መንግሥት፣ Stern magazen እና የአሜሪካ መንግሥት ትልቅ ዕርዳታ አድርገዋል:: በ1984 ዓ.ም. የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን 3,538,690 ኩንታል የሚይዙ 353 መጋዘኖችና 112 ሳይሎዎች ሲኖሩት በአገሪቷ ልዩ ልዩ ክፍል ተሰራጭተው ይገኙ ነበር:: ከነዚህ ማህል ትልቁ በ13 ሚሊዮን ብር የተሰራውና 1,000,00 ኩንታል የሚይዘው ናዝሬት ከተማ ወደ ሶደሬ መሄጃ መንገድ ዳር ያለው ነው::

የወሎ ጠቅላይ ግዛት 1,163,450 ኩንታል የሚይዝ የመጋዘን አቅም አለው:: እነዚህ መጋዘኖች በአሥራ ሁለቱም የወሎ አውራጃዎች ሲገኙ ከዕማማኮ መጋዘኖች 1/3ኛዎቹ መሆናቸው ነው:: ይህ የመጋዘን ይዞታ ተደላድሎ የተከፋፈለ ሳይሆን አብዛኛው 735,750 ኩንታል የመያዝ አቅም የሚገኘው ኮምቦልቻና ደሴ ላይ ብቻ ነው::

## የመጠባበቂያ የምግብ ክምችት

የመጠባበቂያ እህል ክምችት የሚደረገው ለድርቅ ሊጋለጡ የሚችሉ መሆናቸው በጥናትና ከአሁን በፊት በታወቁ ገጠመኞች የተረጋገጡ አካባቢዎች ሲሆን ዓላማውም ችግሩ ሲከሰት የሰው እልቂት ከመድረሱ በፊት ምግብ ማቅረብ እንዲያስችል ነው:: ስለዚህ ገና በ1966 ዓ.ም. ዕማማኮ ሲመሰረት ነበር ጥናት ተዘጋጅቶ ለዕርዳታ ሰጪዎች የቀረበው:: ነገር ግን ከስምንት ዓመት በኋላ በ1975 ዓ.ም. ነበር ለእህል ክምችት የሚውለውን 120,000 ኩንታል የዓለም የምግብ ድርጅት የሰጠው:: ይህም የእህል ክምችት እስከ 1,800,000 ኩንታል ደርሶ ነበር:: ለረሃብ ይጋለጣሉ ተብሎ የሚገመቱትን በአስፈላጊ ጊዜ ለአምስት ወር ስለሚመግብ በዚያ ጊዜ ውስጥ ተጨማሪ እህል በግዢም ሆነ በእርዳታ ስለሚመጣ የሰውን ህይወት ከህልፈት ለመታደግ ይቻላል በሚል ነበር:: 120,000 ኩንታል ግን ይህን ለማድረግ የሚያስችል አልነበረም:: ሁለተኛ

ው ከባድ የረሃብ አደጋ ከአሥር ዓመት በኋላ በ1977 ዓ.ም. ሲከሰት የነበረው መጠባበቂያ 180,000 ኩንታል ብቻ ነበር። ነገር ግን ወሎ ውስጥ 1,166,450 ኩንታል የሚይዝ ማከማቻ አቅም ነበረ። ተጣጥረን ራሳችንን ካልቻልን ምን እና እንዴት መደረግ አለበት የሚለውን ማወቅ ብቻ አይጠቅምም። አምርተንም ሆነ ገዝተን የሚያስተማምን የምግብ ዋስትና እንዲኖር የሚያስችል አቅም መገንባት ያስፈልጋል።

**የአደጋ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ**

ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን የድርቅ አደጋ ለመተንበይና የአደጋውን መጠን ለመገመት የሚችል ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን አግባብነት ያላቸውን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ስብሰባ በመጥራት ስለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናት እንዲያደርጉ የቴክኒክ ግብረሃይል አቋቁሞ፣ የቴክኒክ ሁኔታውን መርምሮ፣ ለአደጋ የተጋለጡ አካባቢዎችን ሁኔታ ለመተንበይ የሚያስችል ዘዴ ፈጥሮ፣ ሁኔታውን የሚከታተልና የሰዎችን የኒውትሪሽን ሁኔታ የሚያጠና አካል የሚቋቋምበትን ዘዴ እንዲያቀርብ አደረገ። የተቋቋመውም ግብረሃይል ይህ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ተቋም በእማማኮ ውስጥ እንዲቋቋም ሃሣብ ስለአቀረበ ይህ አሁን ያለው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በ1970 ተቋቁሞ ሥራውን ጀመረ።

የዚህ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተቋም ዓላማው በድርቅ ምክንያት የሚከሰተው ረሃብ፣ የከፋ አደጋ ከማድረሱ በፊት ለመከላከልና ከደረሰም ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስችል መረጃ መስጠት ነው። በዚህም መረጃ መሠረት በተደጋጋሚ የሚጠቁትን አካባቢዎች ለይቶ በማወቅ ዘላቂ መፍትሄ በማቀድ የረሃብ እልቂት እንዳይደርስ መከላከል እንዲቻል ማድረግ ነው። በተጨማሪ ችግሩ ቢከሰት እንኳ ለችግሩ የተጋለጠውን ሕዝብ ብዛት ለይቶ በማወቅ የሚያስፈልገውን የዕርዳታ መጠንና አይነት አዘጋጅቶ በአፋጣኝ መድረስ መቻል ነው። የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተቋም የሚከተሉት ዝርዝር ሃላፊነቶች ተሰጥተውታል።

1. የምግብ እጥረት የሚከሰትበትን አካባቢ፣ የእጥረቱን መጠንና በእህል እጥረቱ ለአደጋ የሚጋለጠውን ሕዝበ ቁጥር መተንበይ፤
2. የእህል እጥረት ያለበትን አካባቢና ትርፍ የሚመረትበትን አካባቢ ማወቅ፣ እጥረቱ የሕዝቡ መሠረታዊ ምግብ በሆነው የእህል የጥራጥሬና የቅባት እህል ዋጋ ላይ የሚያስከትለውን ሁኔታ መገመት፤
3. የሚከተለውን አደጋ ለመቋቋምና ሊወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ሃሣብ ማቅረብ፤

4. የእህል እጥረትን ለመከላከል የዝግጁነት ክምችት የሚደረግበትንና በአስፈላጊ ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችል መረጃ ማቅረብ፤

5. በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው ጥረት ተሳታፊ የሆኑ ተባባሪ ድርጅቶችና አካላት ሊያተኩሩበት የሚገባውን አካባቢ በማመላከት ድርቅን ለመከላከል የሚያስችሉ የልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ማገዝ።

በእማማኮ አስተባባሪነት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አካል የሆኑት ስምንት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ነበሩ። እነዚህም፣

- የግብርና ሚኒስቴር፣
- የንግድ ሚኒስቴር
- የትምህርት ሚኒስቴር
- የመንግሥት እርሻ ሚኒስቴር
- የማዕከላዊ እስታስትቲክስ ባለሥልጣን
- ብሄራዊ የሜትሪዎሎጂ አገልግሎት ባለሥልጣን እና
- የኢትዮጵያ የኒውትሪሽን ኢንስቲትዩት ናቸው።

የዕማማኮ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የፕላን አገልግሎት አራት ክፍሎች ሲኖሩት ከነዚህ ሁለቱ በቀጥታ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ላይ ያተኮሩ ነበሩ። እነዚህም

1. የእስታትስቲክና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ክፍል ሲሆን የዚህም ክፍል ሥራ ስለ ሰብል ምርት፣ ስለ ኒውትሪሽንና ስለከብቶች ሁኔታና የሰብልና የከብቶችን ዋጋ ጥናት በማድረግ የምግብ ስርጭት ይዘትን መከታተል ነው።

2. የአደጋ ቅድመ ዝግጁነትና አጠቃላይ መረጃ ቡድን ሲሆን ስራውም ለአደጋ የተጋለጡትን አካባቢዎች ዝርዝር ጥናት በማዘጋጀትና ግምገማ በማድረግ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባውን የዝግጁነት ዕቅድ ማዘጋጀት ነው።

የዚህ ፕሮግራም ሲስተም ሥራ የምግብ ሰብሎች በገበያ መገኘ ታቸውን የመለኪያ መስፈርት እንዲሆኑ የተመረጡት አመላካቾች ላይ የሚከሰቱ ለውጦችን መከታተል ሲሆን ለውጦቹም ምግብ አቅርቦት ላይ ያላቸውን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ገጽታ ማወቅና መዘገብ ነው። እነዚህ አመላካች መስፈርቶች (ኢንዲኬተሮች) በአብዛኛው የአቅርቦትና የፍጆታ ፍላጎት ላይ የሚከሰ ተውን የምርት ይዘት፣ የዝናብና የውሃ አቅርቦትን፣ የግጦሽ ሥፍራዎችን የመኖ ይዘት፣ የሕዝቡን የኒውትሪሽን አቋም እና የሕዝብን ፍልሰትና ከቦታ ቦታ የመንጓዝ ሁኔታ የሚመዝኑ ናቸው።

*ይህንንም ለማድረግ፣ ልዩ ልዩ የመረጃ አሀዞች ተሰባስበውና ወደ ሥራ ለመተርጎም የሚያስችል እቅድ እንዲሆኑ ተገናዝበውና ተሰልተው መቅረብ አለባቸው:: የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃን ለማዘጋጀት የአየርና የእርሻ ሁኔታን፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ መረጃዎችን ማሰባሰብና ሕዝቦች ችግርን ለመቋቋም የሚወስዷቸውን እርምጃዎችና ባህላዊ እሴቶችን የሚያካትቱ አሀዞችን ማቀናበር ያስፈልጋል:: ይህንንም ለማድረግ የልዩ ልዩ ሙያ መስኮችን፣ መሥሪያ ቤቶችንና ድርጅቶችን ማካተቱ አስፈላጊ ነበር::*

*ለቅድመ ማስጠንቀቂያ ትንበያ የሚያስፈልጉት ግብአቶች በሙሉ ከልዩ ልዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶችና ከአገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተሰባስበው በወቅቱ ሲደርሱ ጠቃሚና ነፍስ አድን ማስጠንቀቂያ ይሆናሉ::*

*ከመንግሥት ቅድመ ማስጠንቀቂያ በተጨማሪ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግሥታትና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቡድን ጽ/ቤት የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ ያሰራጫሉ:: የዓለም የምግብ ድርጅትም የሰብል ምርትን የሚያጠና ቡድን በመላክ የምግብ አቅርቦት ሁኔታን ያጠናል:: እ.ኤ.አ. በ1983/84 ዓ.ም. የዓለም የምግብ ድርጅት የሚያስፈልገውን የእህል መጠን ሳይሆን ሊጓጓዝ የሚችለውን ታሳቢ በማድረግ 125,000 ቶን እህል ብቻ በዕርዳታ ይጠየቅ በማለቱ በተፈጠረው ውዝግብ ጠቃሚ ጊዜ ሊባክንና የሰው ህይወት ሊጠፋ ችሎ ነበር:: ይኸ ችግር በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ክፍሎች የጋራ ጥናት በማድረግ ከሁሉም የተውጣጣ አጥኚ ቡድን በጋራ ስላሰማሩ በመጠኑም ቢሆን ተሻሽሏል::*

*ይህ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የእርሻ ድርጅትን ትኩረት ስለሳበ ከታንዛንያ የክልል አስተዳዳሪዎችና የግብርና ባለሙያዎች መጥተው ጥናታዊ ጉብኝት በማድረግ ከኛ ልምድ እንዲማሩ አድርጓል:: ቅድሚያ ማስጠንቀቂያውም ምስጋናና አድናቆትን አግኝቷል::*

### 4. በኢትዮጵያ የአደጋ ምክንያቶችና የሚያስከትሏቸው ችግሮች

*በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ የሚደርሰውና ብዙውንም ሕዝብ የሚጎዳው ድርቅ ነው:: በተለይ በተደጋጋሚ የሚጠቁት ከደጋው ክፍል ወሎ፣ ትግራይ፣ ኤርትራ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ጎንደርና ጎጃም ሲሆኑ ከቆላማው ክፍል ሐረርጌ (ኦጋዴን)፣ ሲዳሞ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ባሌና አርሲ ነበሩ:: ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ዛሬ አሥራ አንድ ጠቅላይ ግዛቶች ከባድ የድርቅ ችግር በተደጋጋሚ አጥቅቷቸዋል:: በ1998 ዓ.ም. 7,923,150 ሕዝብ በድርቅ ምክንያት ለረሃብ ተጋልጦ ነበር::*

*በ1979 አሰቃቂ ረሃብ ሲከሰት (መሐመድ አሚን በተለይ የኮረምን መጠለያ ካምፕ በፊልም በቀረጸበት ወቅት) ወደገበያ ቀርቦ የነበረው እህል ለወትሮው ከነበረው ጋር ሲተያይ 50% ብቻ ነበር:: ስለዚህ*

*የእሕል ዋጋ በጣም ናረ፡፡ ገበሬውም ሆነ ከብት አርቢው ለመኖር ሲል ይህንን ውድ እህል ሸማች ሆነ፡፡*

*በዚህ ጊዜ የታየውን የእህል ዋጋ ግሽበት (የዓመቱን አማካኝ ዋጋ በመውሰድ) እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡ የማሽላ ዋጋ በኩንታል 60 ብር የነበረው በ1976 ብር 121 ፣ 1978 ደግሞ ብር 177 ሲደርስ፣ ጤፍ በኩንታል በ1976 ብር 86 የነበረው፣ በ1977 ብር 167 ፣ በ1978 ብር 221 ደርሶ ነበር፡፡ እንዲሁም የገብስ ዋጋ በ1976 ብር 54 የነበረው በ1976 ብር 97፣ በ1998 ደግሞ 139 ደረሰ፡፡ ይሔ ዋጋ ለገበሬውም ሆነ ለአርብቶ አደሩ ካቅሙ በላይ ስለነበረ ከብቱን፣ ጌጣጌጡንና ቅርሱን ለመሸጥ ተገደደ፡፡ ይህም አልበቃ ሲለው ወደ አዲስ አበባ፣ አስመራና ሌሎች መንገድ ዳር ወደ አሉ ከተሞች መሰደድ ጀመረ፡፡ የመንገድ ዳር መጠለያ ጣበያዎች እንደገና ተቋቋሙ፡፡*

*ምንም እንኳን የኮረም ጣቢያ ከ1975 ጀምሮ ቢኖርም ብዙዎቹ ጣቢያዎች ከ1977 ጀምሮ ነበር የተቋቋሙት፡፡ ከጥር ጀምሮ በወር 2,000 ሰው ወደ ኮረም መመገቢያ ጣቢያ መጉረፍ ጀመረ፡፡ በጥቅምት 1976 ዓ.ም. የባቲና የሀርቡ ጣቢያዎች እንደገና ሥራ ጀመሩ፡፡ በጥር 1976 እና በየካቲት 1985 ሚሌ ላይም የመመገቢያ ጣቢያ ሥራ ጀመረ፡፡ ወሎ ድርቁ የከፋ ከመሆኑ የተነሳ በ1978 ከነበሩት 60,000 ተረጂዎች ግማሾቹ ከወሎ ነበሩ፡፡ የድርቁ ሁኔታ እየከፋ በመምጣቱ ሚያዝያ 1978 በመጠለያ የነበረው ሕዝብ ብዛት 282,000 ደርሶ ነበር፡፡*

*በዚህ ወቅት የሞቱ ሰዎች ቁጥር በሚገባ አልተመዘገበም፡፡ በጣም የተጠቁት አውራጃዎች አምባሰል፣ ቃሉ፣ ራያና ቆቦ፣ አውሳና የጁ ሲሆኑ በ1977 እና በ1978 በመጠለያ ጣቢያ የሞቱት ሰዎች በግምት 60,000 ደርሶ ነበር፡፡ ይህ አሃዝ መጠለያ ውስጥ ካለው 7% ሲሆን በአጠቃላይ የሞተው ሰው ቁጥር በትክክል ባይታወቅም ከ60.000 በላይ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በአማካይ በመጠለያ ከነበሩ ሰዎች የሚሞቱት ቁጥር ከአንድ ሺው ሃያ አምስት ነበር፡፡*

*ሰዎች ለሠፈራ እሚመለመሉበት የአምባሰል መቀበያ ጣቢያ ውስጥ 891 ሰዎች ሲሞቱ ለጉዞ በሚዘጋጅበት ጣቢያ 900 ሰዎች ስላለቁ ድምሩ 1,791 ደርሶ ነበር፡፡ ይኸ ከአምባሰል ወደ ሰፈራ ከሄዱት መሐል 4.2% መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት 372,298 ከሚሆኑት የወሎ ሰፋሪዎች ማህል የሠፈራ ሕይወታቸውን ከመጀመራቸው በፊት 15,000 ያህል እንደሞቱ ይገመታል፡፡ በጠቅላላ በወሎ ከ1966 እስከ 1978 ድረስ በረሃብ የሞተው ቁጥር 300,000 ይደርሳል የሚል ግምት አለ፡፡*

**የሞት ምክንያቶች**

*ተረጂዎቹ የሞቱበትን ምክንያት ለማወቅ ልዩ ልዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ሁኔታውን ለመገንዘብ እንዲረዳ አንዳንዶቹን ማየቱ ይጠቅማል፡፡*

*ወርልድ ቪዥን ሳንቃ ላይ ባደረገው ጥናት መሰረት ከሞቱት መሐል 51% በተቅማጥ ሲሆን 11% በኒሞንያ ነበር፡፡ በባቲ መጠለያ*

ከሞቱት 707 ሰዎች ማህል የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል በየካቲትና በመጋቢት 1978 ባደረገው ጥናት 47% የሚሆኑት በተቅማጥ 22% በኒሞንያ 19% በሃይድሬሽን 4% በማልኒውትሪሽን እና 3% በወባ እንደሆነ አሳይቷል። በዚህ መሠረት ተቅማጥ፣ ኒሞኒያና ኩፍኝ ከፍተኛ የሞት ምክንያቶች ሲሆኑ የምግብ ችግር ተከታዩ ምክንያት ነበር። ከነዚህ በተጨማሪ እንደ ታይፈስ፣ ታይፎይድ (influenza)፣ ትኩሳት፣ ሚኒንጃይትስና ሂፐታይተስም በወሎ ከተከሰቱ የሞት ምክንያቶች መሐል ይገኙበታል።

### 5. የ1976 ድርቅና የሰብል መጥፋት ማስጠንቀቂያ

ከ1977 ጀምሮ በድርቅ ምክንያት ምርት አለመገኘቱ በተደጋጋሚ ተገልጾ ለዕርዳታ ሰጪዎች ዕርዳታ እንዲያደርጉ ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም ድጋፉ ይኸን ያህል አልነበረም። በኢሴኤ አዳራሽ በ1974 ዓ.ም. የተባበሩት መንግሥታት ባደረገው ስብሰባ ላይ የዕርዳታና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ድርቅ መጠቃቱዋን አስመልክቶ ጊዜያዊ ዕርዳታ ብቻ ሳይሆን የችግሩ መነሻ በልማት ኋላ ቀር መሆናችን መሆኑና በርሻ፣ በውሃ ሃብት ልማትና በመሬት ልማት አለመሟላት ስለነበረ ችግሩን መቅረፍ የሚያስችል የልማት ዕርዳታና ብድር ማስፈለጉን የሚገልጽ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርቦ ነበር።

በመላው አገሪቱ የመኸር ዝናብ ከዘወትር መጠኑ ከግማሽ በታች መሆኑ ሪፖርት በ1976 ዓ.ም. ተደርጎ ነበር። ከዚህም የተነሳ በብዙ አካባቢዎች አንዳንድ ከአመት አመት የሚፈሱ ወንዞችና ምንጮችም ደረቁ። አርብቶ አደሮችም ውሃና ግጦሽ ፍለጋ ተሰደዱ። የዓመቱ የትምበያ ሪፖርት 5.2 ሚሊዮን ሕዝብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ገለጸ። ሁኔታው እያደር ተባብሶ የዕርዳታ ፈላጊው ቁጥር በታህሳስ 1976 ወደ 7,750,000 ከፍ ብሎ ነበር። ለዚህም የሚያስፈልገው የዕህል መጠን 1,504,775 ቶን ነበር። በመጋዘን የነበረውና ቃል የተገባለት እህል 220,490 ቶን ሲሆን የተጠየቀው ዕርዳታ 1,284,285 ነበር። ከተረጂው አንድ ሦስተኛው ማለት 2,587,420 ህዝብ ወሎ ነበር። የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅትም ባደረገው ግምት የእህል ሰብል በ25% ጥራጥሬ በ30% እንደሚቀንስና 7.3 ሚሊዮን ቶን ከሚሆነው ምርት ከ1.7 እስከ 2 ሚሊዮን ቶን ምርት ስለቀነሰ ከ6.5 ሚሊዮን እስከ 8 ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ ዕርዳታ እንደሚፈልግ ተገልጾ ነበር። ዕማማኮ ካቀረበው ሪፖርት ጋር ተመሳሳይ ነበር። ቢሆንም ባለው የወደብ ሁኔታና የትራንስፖርት አቅም ማነስ ምክንያት ሊጓጓዝ የሚችለው እህል ስላነሰ ዕርዳታ ሰጪዎቹ የዓለም የምግብና እርሻ ድርጅት የኛን ጥናት እስኪያረጋግጡ በመቆየታቸው የሰው ሕይወት ማለፍን አስከተለ።

### ፮. የችግሩ ገፈት ቀማሽ የወሎ ክፍለ ሃገር ህዝብ

በተለይ በ1976/77 ዓ.ም. በደረሰው ድርቅ ወሎን በጥልቀት መመልከቱ ችግሩን ለመገንዘብና ለወደፊት እርምጃችን ሊረዳ ይችላል። በሰሜን ምሥራቅ የሚገኘው የወሎ ክፍለ ሃገር አሥራ ሁለት አውራጃዎች ነበሩት። ክፍለ ሀገሩ በአብዛኛው ደጋ ነበር። ይሁንና በአውሳ አውራጃ የሚገኘው የደንከል ስምጥ ከባሕር ወለል በታች ነው። በአገራችን የሚታወቁት ሦስቱም አየር ንብረቶች (ማለትም ደጋ፣ ወይናደጋና ቆላ) ይገኙበታል።

በአፋር ክልል ከሚገኘው አርብቶ አደር ማለት ከአውሳ አውራጃ በስተቀር ሌሎቹ የእህል ሰብል አምራች የሆኑ የገበሬዎች መኖሪያ ናቸው። የወሎን ለአደጋ ተጋላጭነት ሁኔታ ያጠኑት የእርሻና የአካባቢው የተክልና የእጽዋት ይዘት አካባቢዎችን (Agro-ecological zones) ሲከፋፍሉ ሁለት መስፈርቶችን በመጠቀም ነው። (1) የእህል መብቀያውን ወቅት እርዝማኔ እና (2) ከባሕር ወለል በላይ ያለውን ከፍታ በመጠቀም ነው።

ከአውሳ በስተቀር በዝናብ በቀል እህል ሰብል የሚተዳደሩትን አውራጃዎች የአፈር ጥልቀት በማጥናት ከ35 ሲ. ሜትር ያነሰ አፈር ያለው ከወሎ 90% ሲሆን የአገር አቀፍ አሃዝ ግን 35% መሆኑን አሳይተዋል። ከላይ ካለው አፈር በያመቱ 1.3 ሲ. ሜትር በዓመት እየታጠበ ይሄዳል። እስከ 2010 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የአፈር መከላት ሁኔታ የሚከተለውን ይመስላል።

| የአፈር ጥልቀት | 1985 | 2010 |
|---|---|---|
| ከ150 ሴሜ በላይ | 9% | 9% |
| 100 ሴሜ - 150 ሴሚ | 11% | 11% |
| 50 - 100 ሴሚ | 28% | 23% |
| 25 - 50 ሴሚ | 19% | 14% |
| 10 - 25 ሴሚ | 21% | 7% |
| 0 - 10 ሴሚ | 10% | 24% |
| ዲንጋያማ | 2% | 12% |

በ1977 ዓ.ም. የወሎ ሕዝብ ብዛት 3,609,918 ሲሆን በአማካይ በቤተሰብ በቃሉ 4.4 በዋግ፣ ላስታና አምባሰል 4.2 በዋድላ፣ ደላንታ ራያና ቆቦ 4.1 በየጁ፣ አውሳ፣ ቦረናና ወረኢሉ 4.4ና በወረሂሙኑ 3.9 ሰው ይገኝበታል። ከሕዝብ ቁጥር መብዛት የተነሳ ተራራውንና ምርታማ ያልሆነውንና አፈሩ የታጠበና በቂ ዝናብ የማይገኝበትን አካባቢ ጭምር ያርሳሉ። ከዚህም የተነሳ መሬቱን በመከፋፈል ከሄክታር ያነሰና ሊያኖር የማያስችል መሬት ባለይዞታ ሆነዋል።

ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ ከወሎ ሕዝብ ከፊሉ ተረጂ ሆኗል። ከወሎ ሕዝብ በተከታታይ ዓመታት ተረጂ የነበረው በ1970 ዓ.ም. 24.3% በ1971 ዓ.ም. 39.1% በ1972 ዓ.ም. 36.4% በ1973 14.4% በ1974 ዓ.ም. 20.8% በ1975 ዓ.ም. 31.1% በ1976 ዓ.ም. 49.2% በ1977 ዓ.ም. 61.1% በ978 ዓ.ም. 40.1% በ1979 8.3% እና በ1980 ዓ.ም. 20.9 ነበር። ከዚህ

ሁኔታ የምንረዳው የወሎ ሕዝብ ለድርቅ የተጋለጠ መሆኑን ነው:: ከላይ በተጠቀሱት አስር አመታት የተጎዳው ሕዝብ በአማካይ ከመቶ ሰላሳ ሁለት እጅ ነበር:: ምንም እንኳን በ1979 ዓ.ም. ወደ 8.3% ዝቅ ቢልም በዓመቱ መልሶ 20.8% ገባ::

ወሎ በአብዛኛው ተራራማና መንገድም የሌለው ስለነበረ ችግር መኖሩ ከታወቀ የዕርዳታው እህል ክረምት ከመግባቱ በፊት አመቺ ቦታዎች ገብቶ መከማቸት አለበት:: ከአዲስ አበባ መቀሌ ከኮምቦልቻ አሰብ ባሉት መንገዶች ዳር የአሉት ከተሞች በችግር ጊዜ ወደ ውስጥ ገብቶ የሚኖረው ሕዝብ እርዳታ ፍለጋ የሚወጣባቸው ናቸው::

**፯. ለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃ የተወሰደ እርምጃ**

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በ1974 ዓ.ም. ዝቅተኛ ልማት ያላቸው አገሮች ጉዳይ የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ አዲስ አበባ ላይ ሲደረግ ዕማማኮ ለዕለት ደራሽና ለዘለቄታ ልማት የሚያግዙ የቁሳቁስና የገንዘብ ዕርዳታ ጠይቆ ነበር:: ከዚያም በመቀጠል በ1975 እና በ1976 ተመሳሳይ ጥያቄዎች ቀርበው ነበር:: ቢሆንም ምላሹ አመርቂ አልነበረም::

በ1977 ችግሩ ተባብሶ አርሶ አደሩ ቀዬውን ለቆ ምግብ ፍለጋ ተሰደደ:: አርብቶ አደሩም ለራሱ ምግብ፣ ለከብቶቹ ግጦሽ ፍለጋ ከብቱን እየነዳ በየአቅጣጫው ወደ ደጋው መጓዝ ጀመረ:: በዚያን ጊዜ ዕርዳታ ሰጪዎች ዕርዳታ ፈላጊ ለነበረው 5.2 ሚሊዮን ሕዝብ ዕርዳታ ለመስጠት ቃል ቢገቡም ከአምስት ወር በኂላ እርዳታው አልደረሰም:: እንደገና አሁንም ችግሩ ተባብሶ በአገሪቱ በሙሉ የተረጂው ቁጥር

*6,098,011 ሲደርስ፣ በመጠለያ ሰዎች እንዳይሞቱ አስቸኳይ የእርዳታ ጥያቄ ለ400,000 ቶን ቀረበ።*

*ጥያቄው በራስ አቅም በቅድመ ማስጠንቀቂያ መሠረት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ካልተቻለ፣ መንገዱና ተሽከርካሪው ኖሮ እርዳታው በወቅቱ በሚፈለግበት አካባቢ በመጋዘን ካልተከማቸ ጥሩ መረጃ መኖሩ ብቻ ችግሩን ሊፈተው አለመቻሉ ነው።*

**ራስን መቻል ቁልፍ ነው**

*ዕማማኮ ሲጨንቀው የመገናኛ ብዙሃንን በመጥራት ሁኔታውን ለአለም ሕዝብ እንዲያስረዱ ጋበዘ። በሰኔ 1970 ወይዘሮ ሁኔን ሎር ጋዳሽ በጀርመን ቴሌቪዥን ሪፖርት አቀረቡ። በቢ.ቢ.ሲ.ም* "Seeds of Despair" *የሚባለውን ፊልም ቻርለስ ስቱዋርት አቀረበው። አራት ደቂቃ የሚቆየው መሐመድ አሚን ያነሳው ፊልምና ማይክል ቦርክ ገለጻ ያደረገበት ዜና በቢ.ቢ.ሲ. ሲወጣ የችግሩ አስከፊነት በየሰው ቤት ገብቶ ታየ። የብዙዎች ልባቸው ተነካ። እነሱም የሚችሉትን ሰጥተው መንግሥታቶቻቸውን ደግሞ እንዲረዱ ጫና ፈጠሩ። በተለይ አንድ ቤተሰብ ያላቸውን ቤት በመሸጥ የኢትዮጵያውያንን ነፍስ ለማዳን መስዋእትነት ከፈሉ።*

*በ1977 ዓ.ም. በ10 ክፍለ ሃገሮች በ64 አውራጃዎች 283 የእህል ማደያ ጣቢያዎች እየሰሩ ነበር። በአመቱ በ68 አውራጃዎች እና በ310 ማደያ ጣቢያዎች ዕርዳታ መሠጠት ቀጠለ።*

*ዕርዳታ የሚሰጠው በድርቅ ለተጎዱ ብቻ ሳይሆን ከውጪ በተሰነዘረ ጦርነትና በእርስ በርስ ውጊያ ለሚፈናቀሉ፣ ከጅቡቲና ከሶማሌ ከስደትና ከምርኮ ወደ አገራቸው ለሚመለሱትም ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ከአራት መቶ ሺህ የሚበልጡ የሱዳንና የሶማሌ ስደተኞችንም የመርዳት ጫና ነበረ።*

*አስረኛውን የአብዮት በዓል ለማክበር በሚያደርገው ወጪና ዝግጅት ምክንያት ለችግሩ በቂ ትኩረት አልሰጠውም በማለት በወቅቱ በነበረው መንግሥት ላይም የሰላ ትችት ተሰነዘረበት። መንግሥት ከበአሉ ማግሥት ጀምሮ ሁኔታውን ለማስተካከል በወቅቱ መሪ ሰብሳቢነት ትልቅ ቡድን አቋቁሞ በውስጡም 12 ንዑሳን ኰሚቴዎች በከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሊቀመንበርነት አዋቀረ። እነዚህም የዕለት ዕርዳታ፣ የሎጂስቲክና ትራንስፖርት፣ የሕዝብ ማስፈር፣ የእርሻ፣ የመንግሥት እርሻ፣ የኰንስትራክሽንና የውሃ ልማት፣ የፕላንና ፕሮግራም፣ የኢንስፔክሽንና የመረጃ፣ የፕሮፓጋንዳና የፀጥታ ከሚቴዎች ነበሩ።*

*የተባበሩት መንግሥታትም ዕርዳታ የሚያስተባብር ኃላፊ በረዳት ዋና ፀሐፊ ደረጃ በካምፑቺያ የነበረውን ችግር ለመፍታት በተደረገው እንቅስቃሴ የማስተባበር ልምድ የነበራቸውን የፊንላንድ ዲፕሎማት ኩርት ያንሰንን ሾመ።*

*ሕዝብ ቀዬውን ለቆ በየመጠለያ ጣቢያው ተሰዶ ባለበት ወቅት (ሻለቃ ዳዊት የወቅቱ ኮሚሽነር ቀይ እምባ በተባለው መጽሐፋቸው*

እንደገለጹት)፣ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1984 ዓ.ም. በፌብርዋሪ መጨረሻ በመጠለያና በእህል ማደያ ጣቢያዎች በየመንደሩ በሳምንት 10,000 ሰዎች ከማርች በኋላ ከ16,000 እስከ 17,000 በሳምንት የሚሞትበት ሁኔታ ነበር:: መንግስት፣ የተባበሩት መንግሥታትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መረባረብ ጀመሩ::

**የእስት ዕርዳታ ስርጭት**

አብዛኛው የአገራችን ክፍል የመንገድ መገናኛ ስለሌለው ዕርዳታ ማዳረሱ ፈታኝ ችግር ነበር:: የትግራይ ጠቅላይ ገዥ የነበሩት ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም አውራጃን ካውራጃ ለማገናኘት ባደረጉት ጥረት (ጥርጊያም ቢሆኑ እንኳ) በተሰሩት መንገዶች ምክንያት በትግራይ ዕርዳታ የማሰራጨቱ ሥራ የተሻለ ነበር:: በወሎ ከባድ የመንገድ ችግር ከመኖሩ የተነሳ አብዛኛው እርዳታ የተከፋፈለው መንገድ ተከትሎ ባሉት ከተሞች ስለነበር አብዛኛው በምዕራብ ያለው የደጋው ተራራማ አካባቢ በሚገባ አልተረዳም:: ላስታን ዋድላ ደላንታንና ቦረናን የመሳሰሉት አካባቢዎች መንገድ ስለሌላቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች 62% የሚሆነውን የእርዳታ እህል በ1985 ዓ.ም. ያከፋፈሉት በሦስቱ አውራጃዎች ማለት በአምባሰል፣ የጁና ራያ ቆቦ ብቻ ነበር:: በነዚህ አውራጃዎች የነበሩት ተረጂዎች ዕርዳታ ከሚያስፈልገው ሕዝብ 34% ብቻ ነበሩ:: ይህ ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ ነው:: ምክንያቱም በጥር 1985 ዕማማኮ ከተረጂው 68% ሲሸፍን ቢቆይም ዕርዳታ ሰጪዎች አብዛኛውን ዕርዳታ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል ማሰራጨት ስለጀመሩ በታህሳስ 1985 የዕማማኮ ሽፋን 12% ብቻ ነበር:: የመሠረተ ልማት አውታር የሆነው መንገድ ካልተሰፋፋ በድህነት ላይ የምናደርገው ጥረትም ሆነ ችግር ሲከሰት ለመርዳት የሚደረገው እንቅስቃሴ ውጤታማ ሊሆን አይችልም::

በ1984/85 በወሎ ዕርዳታ ከሚያስፈልገው 1,790,840 ከሚሆን ሕዝብ መሐል እርዳታ የደረሳቸው 1,447,282 ናቸው:: ይኸም የተሰራጨው በ21 መጠለያ ጣቢያዎች (የሠፈረ መጠለያዎችን ጨምሮ) በ187 የእህል ማደያ ጣቢያዎች እና በ38 መመገቢያ ጣቢያዎች ሲሆን የተሰጣቸውም 414,357.77 ኩንታል እህል 32,929.09 ኩንታል አልሚ ምግብና 2,100 ኩንታል የሚበላ ዘይት ነበር::

ይህን ዕርዳታ ለማድረስ ዕርዳታ ሰጪዎቹ ባላቸው የቢሮክራሲ መንተት የተነሳ ፈታኝና አስጨናቂ መዘገይቶች ስለሚፈጠሩ ስምምነት የተደረገበት የምግብ ዕርዳታ ከአውሮፖ የጎን ገበያም ሆነ የዓለም ምግብ ድርጅት ለተጠቃሚው ለመድረስ እስከ ሰባት ወር ይፈጅ ነበር::

**ሎጂስቲክስ**

በየወደቦቻችን የነበረው የቢሮክራሲ አሠራር (ለምሳሌ ለአንድ ዕቃ እስከ 42 ፎርማዎች ማስፈለጉ) ለእርዳታ መዘግየት ተጨማሪ ምክንያት ነበር። በተሽከርካሪም በኩል በየወሩ ሃምሳ መኪናዎች ያህል መሰናከላቸውና አራት ወይም ስድስቱም የመኪና እግር ላይ የሚገጠሙት ጎማዎች በአመት አራት ጊዜ በአዲስ መተካት ስለነበረባቸው በጎማ እጦት ምክንያት መኪናዎች ለሥራ ዝግጁ አለመሆን ሌላው ችግር ነበር። የምንጠቀምባቸው መኪናዎችም 47 ዓይነትና ከመቶ ሞዴል በላይ መሆናቸው በመለዋወጫ አቅርቦት በኩል ተጨማሪ ፈተና ነበር። የመኪና ምርጫና በጥራት ተመርጠው አለመምጣት የሚያስከትለውን ችግር ለማስረዳት ያህል ከኩዌት በአስቸኳይ ከመጡት መቶ ተሽከርካሪዎች ከአመት በኋላ ሁሉም ሥራ ላይ ሊውሉ አለመቻላቸውን መገንዘቡ ብቻ በቂ ነው።

## ፩. በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መሠረት የሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ የሚታዩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች

*የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተቋም መደራጀቱ በጣም ጠቃሚ ነው። ጥቅሙ እርዳታ ለመጠየቅ የሚረዳ አሃዛዊ መረጃ ማግኘቱ ሳይሆን ሕዝቡን ያለበት ሁኔታ አውቆ የሚያስፈልገውን መፍትሄ ለመቀየስ ማስቻሉ ነው።*

*ባለመታደል አቅም አጣን እንጂ አቅም ብንገነባ ኖሮ ራሳችን ራሳችንን እንድንረዳ የሚያግዘን መሣሪያ ነበር። የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሪፖርት በመኸርም ሆነ በበልግ ያለውን የሰብል ሁኔታ በመተንተን በቂ ምርት እንዳለን ወይም እንደሌለን በወቅቱ ይገልጽ ነበር። ይህም ጠቃሚ ነበር።*

*በዚህም ሪፖርት የእህል እጥረቱን መጠን፣ እጥረቱ የደረሰበትን አካባቢና ምን ያህል ሰው የእህል አቅርቦት እንደሚፈልግ ያሳውቃል። በሪፖርቱ መሠረት የዝግጁነት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። በኛ አገር ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ በመውሰድ ፈንታ እርምጃውን ለመውሰድ የሚያስችሉንን መሣሪያዎች፣ እህል አልሚ ምግብ የትራንስፖርት መኪና፣ ገንዘብ፣ የልማት መሣሪያዎች ፍለጋ፣ ለመንገድ ሥራ፣ ለውሃ ቁፋሮ፣ ለመስኖ ሥራ ወደ እርዳታ ሰጪዎች ለጥያቄ እንሄዳለን።*

*የመጠባበቂያ የምግብ ክምችት አቅማችን የተጠናከረ አይደለም። ለሱም ቢሆን ዕርዳታ ጠያቂዎች ነን። ጥሩ ዝናብ ዘነበም አልዘነበ አሁን ባለን የማምረት አቅም ለሸማችም ሆነ ለተረጂ መቅረብ ያለበትን የእህል መጠን ለማቅረብ ወይም የምርት አቅማችንን ለማሻሻል ወይም ከሌላ ልማት ሥራችን በምናገኘው ገንዘብ ሸምተን ለማቅረብ ልዩ ጥረት ማድረግና መፍትሄ መፈለግ አለብን። ከመሠረቱ ላለው የእህል እጥረት (እስትራክቸራል ዴፊሲት ለምንለው) መፍትሄ መፈለግ አለብን።*

*በ1971 በደረሰው የእህል እጥረት በጥናታችን መሠረት ሊኖረን ከሚገባው የመጠባበቂያ 180,000 ቶን ውስጥ የነበረን 18,000 ቶን (10%)*

ብቻ ነበር። ለትራንስፖርት ኪራይ፣ ለመኪና መግዣ፣ ለነዳጅና መለዋወጫ እህሉን አጓጉዞ ለሕዝብ ለማድረስ 267,757,549 ብር ጥያቄ ለለጋሾች ማቅረብ ነበር ሥራችን።

ከቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በተገኘው መረጃ መሠረት በድርቁ ለሚጎዳው 7.75 ሚሊዮን ሕዝብ ለሕክምና ፍላጎት የሚያስፈልገንን 31,000,000.00 ብር ለማግኘት አሁንም ዕርዳታ ሰጪዎችን ጠይቀን መልስ መጠበቅ ነበረብን።

የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሃዞች ጠቃሚ መረጃዎች ቢሆኑም ዝግጁነትን ማረጋገጥ በሌሎች ችሮታና በጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነበር። ከኛ በኩል በቂ በጀት አልተመደበም። ለዓመታት የዕማማኮ በጀት እርዳታ ለማድረስ፣ ለመጫን፣ ለማውረድ እንኳን የማይበቃ በየዓመቱ 10,000,000.00 ብርና ለአንዳንድ የልማት ሥራዎች የሚሰጥ አነስተኛ ድጎማ ነበር። ስለዚህ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ውጤት የሚኖረው ለዝግጁነት የሚረዳ የገንዘብና የቁሳቁስ አቅም ሲኖር ብቻ መሆኑ ትልቅ ትምህርት ሊሆን ይገባል።

በ1977 ዓ.ም. የተከሰተው ከባድ ረሃብ የተባባሰው አስተማማኝነቱን የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት እያወቀው የኛን የቅድሚየ ማስጠንቀቂያ መረጃ ሎጂስቲኩ የላችሁም በሚል ስላንተተው ነው። በመጨረሻም በመጠኑም ቢሆን ተግባራዊ የሆነው እርዳታ የተገኘው የመገናኛ ብዙሃንና ሕዝቦች በመንግሥቶቻቸው ላይ በፈጠሩት ጫና እና እነቦብ ጊልዶፍ ተሰባስበው በዘመሩት መዝሙር ግፊት ነበር። ነገር ግን ባለው ሎጂስቲክ ሊጓጓዝ የሚችለውን ያህል እንኳን እህል በወቅቱ ቢለቀቅ ኖሮ ብዙ ህይወት ይድን ነበር።

የሎጂስቲክ ችግር መኖሩ የማይካድ ነው። በቅድመ ማስጠንቀቂያ መሠረትና አይ.ኤም.ኤፍ ባጠናው መሠረት ለዘጠኝ ወር የሚያስፈልገው እህል መጠን 912,212 ቶን ቢሆንም ዕርዳታ ማስተባበሪያ ይቻላል የሚለውን መጠን ገዝቶ ጥያቄውን በግማሽ ቀንሶ 450,000 ቶን ሲያደርገው FAO/WFP ግን 125,000 ቶን ላይ ረጉ። አሰብ ላይ ከመርከብ የማውረድ አቅማችን በቀን 2,846.5 ቶን ሲሆን ከወደብ የማንሳት ችሎታችን 2,585.6 ቶን ነበር። ስለዚህ ከመርከብ ወርዶ ማንሳት የማንችለው በቀን 260.9 ቶን በዓመት 93,912 ቶን ቢሆንም የዕማማኮ የችሎታ ግምት ወደ እውነቱ የተጠጋ ነበር። ለማንም መንግስት ቢሆን የራሱን ሕዝብ መመገብ አቅቶት በረሃብ ይሙቱ አይሙቱ ለሚለው ጥያቄ መልሱ በውጪ ሰዎች በጎ ፈቃድ ላይ መሆኑ በጣም አሳሳቢና አጣብቂኝ ነው።

ለዚህ ነው በ1966 ዓ.ም. አስተማማኝ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ፕሮጀክት ሀሣብ የቀረበው። የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅትና የዓለም ምግብ ፕሮግራም ፈቃደኛ ሆነው እገዛ ሲጀምሩ በዕማማኮ ሥር ተቋቋመ። የአስቸኳይ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ፕሮጀክት ዓላማም:-

የተፈጥሮ አደጋ ማለትም በአስከፊ ድርቅ፣ በፀረ-ሰብል ተባይ ወረርሽኝ ... እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ሊከሰት ስለሚችል የዕህል

ክምችቱ አመቺ (እስትራተጂክ) በሆኑ ሥፍራዎች ተቀምጦ በፍጥነት ሊደርስ የሚችል መሆን አለበት። ባልተጠበቀና ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ ወይም የሰው ሠራሽ ችግሮች ማለትም በጦርነት ወይም በመርከብ የተጫነ እህል በማዕበልና በሌላም ችግር ሲዘገይ እርዳታ ሊደርስ የሚችለውን የምግብ እጥረት ለመቋቋም እንዲቻል የታቀደ ነበር። የዕርዳታ ተስፋና የመግዛት አቅም ኖሯቸው ጊዜ በመግዛት ሕይወት በማዳን ለሚሠሩ ድርጅቶች በብድር መልክ የሚሠራጭና ሊተካ የሚችል ክምችት መያዝ ነበር።

ይህም ዓላማ ለረሃብ የሚጋለጥ እስከ ሰባት ሚሊዮን ሊደርስ የሚችል ሕዝብ መጠን ያገናዘበና የሰው ሕይወት ሳያልፍ ተመጣጣኝ ዕርዳታ ከአምስት እስከ ሰባት ወር የርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የተቋቋመበትን ዓላማ ለመወጣት የሚያስችል የአደጋ ዝግጁነት ነበር። በዚያን ጊዜ በነበረው ሁኔታ መሠረት የተደረገው ጥናት የረጂዎችንም የመደገፍ አቅምና በጎ ፈቃድ ያገናዘበ ነበር። በ1967 ተጀምሮ በአምስት አመት ውስጥ የሚከማቸው እህል 180,000 ቶን ይደርሳል። ለአደጋ ይጋለጣል ተብሎ የሚገመተው ሕዝብ ብዛት ከሰባት ሚሊዮን ስለማይበልጥና ሁሉም ባንድ ጊዜ ችግር ላይ ስለማይወድቁ የባሰበትን ሕዝብ ደረጃ በደረጃ በመርዳት የሰው ህይወት ሳያልፍ ተጨማሪ እህል በግዢም ሆነ በዕርዳታ ይደርሳል ተብሎ የታሰበበትን ጊዜ ያገናዘበ ነበር። ይሁንና አፈጻጸሙ እንደታሰበው አልነበረም።

ምንም እንኳን የመጠባበቂያ እህል ክምችቱ ዘግይቶ ቢጀምርም ከዕርዳታ ሰጪዎች 42,500፣ ከመንግሥት ደግሞ 50,000 ቶን ስለተሰጠ የመጠባበቂያ ክምችቱ በ1980 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ 92,500 ቶን ደርሶ ነበር። በአገሪቱ በተደጋጋሚ ይደርስ በነበረው ድርቅና ረሃብ ምክንያት ለክምችቱ ቅድሚያ ተሰጥቶት የታቀደው 180,000 ቶን እንዲደርስ አለመደረጉ ብቻ ሳይሆን በየግዜው ለሚደርሰው አደጋ ከክምችቱ ወጪ የተደረገውም እህል በጊዜው ስለማይተካ የታሰበው ጣሪያ ሊደርስ አልቻለም። በዚህም ምክንያት በሰባት ዓመት ጊዜ ፕሮጀክቱ ሊያከማች የቻለው የዕቅዱን 51% ብቻ ነበር። በ1979 እና በ1980 ዓ.ም. የደረሰውን አስከፊ ድርቅ ለመቋቋም 46,500 ቶን እህል ወጥቶ በመታደሉ ብዙ ነፍስ ድኗል። ቢሆንም ለክፉ ቀን ሊኖረን የሚገባ የመጠባበቂያ ክምችት እህል 180,000 ቶን ሳይሆን 46,000 ቶን ብቻ ነበር። በዚህም ምክንያት የመጠባበቂያ ክምችት እንዲኖረን ስናስብ ሊረዱ የሚችሉ ወገኖችን ድጋፋቸውን በተደጋጋሚ ጠይቀናል።

የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ሀላፊነት በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ የተጋለጡትን ወገኖች መርዳት ስለነበረ ኮሚሽኑ ለሸማቹ ሕዝብ ሀላፊነት አልነበረበትም ነበር። በአብዮቱ ወቅት አያሌ ግብታዊ ውሳኔዎች ተወስደው ነበር። ለምሳሌ፣ በሰቲትና በሁመራ የግል ሀብታቸውን በማፍሰስ በሰሊጥና በማሽላ እርሻ ተሰማርተው የአገሪቱን የዕርሻ ምርታማነት በማሳደግ ላይ የነበሩ ኢትዮጵያውያንን ቅስም የሚሰብር የውርስ አዋጅ ሲታወጅ በኃይል ስለመታቸው ትርፍ ሳይሆን ወጪያቸውን ለመመለስ እንኳን በማይችሉበት ሁኔታ የባንክ ባለዕዳ

አድርጓቸው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በኤርትራ አሳሳቢ የረሃብ ሁኔታ እያንዣበበ ስለነበረ አንድ ኩንታል ማሽላ በ12 ብር ሂሳብ ለልማት ለተሰለፉት ወገኖች ቢበዛ ወጪአቸውን እንዲሸፍን 250,000 ኩንታል በላይ ማሽላ በመግዛት ወደ ኤርትራ ጠቅላይ ግዛት እንዲጓጓዝ በማድረግ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መምታት ተችሎ ነበር፡፡ አንዱ ወፍ ለም መሬት ለማልማት የወጣው ሀይል ሁለተኛው ወፍ በወንድማማች ጦርነት አስመራ ጭምር ከሃያ ኪሎሜትር በማይበልጥ ቀለበት ውስጥ ገብቶ ለነበረው ለአስመራ ከተማና ለየአውራጃዎቹ ሸማች ሕዝብ የሚቀርብ እህል በእህል ሰብል ገበያ በኩል ለሸማቹ በዕማማኮ በኩል ለተረጂው ሕዝብ ማዳረስ ተችሎ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በቀጥታ ለክምችቱ የሚውለው እህል ከውጪ ቢመጣም ከላይ በጠቀስኩት ሁኔታ የሚገኘው እህል የአስቸኳይ ጊዜ መጠባበቂያ ክምችት እህል አጋዥ ነበር፡፡

የኤርትራን የእህል ስርጭት ካነሳሁ አልቀረ በአሊጊደር እና በተሰነይ አካባቢ የነበረው የባራቶሎ የጥጥ እርሻ ይመረት የነበረውን የጥጥ ምርት እርሻ ለማሰናከል የግድቡን ውሃ ወደ እርሻው የሚወስደውን የተሰካ በርሚል የሻቢያና ምናልባትም የጀብሃ ተዋጊዎች በጥይት ወንፊት አድርገውት የነበረውን በአዲስ በመተካት ለትርፍ ቢፈለግ ጥጥ መትከል በገንዘብ አትራፊ ቢሆንም ሕዝብ ለማዳን ግን ሲባል እማማኮ ማሽላ በመዝራት ከዚህ የሚላከውን እህል በተባበሩት መንግሥታት በተሰጠንና የተባበሩት መንግሥታትንም አርማ አድርገው የሚጓዙ መኪናዎችን ከእነ እህሉ ጀብሃና ሻቢያ ሲያቃጥሉ ሕዝቡን ከሞት ለማዳን ከባድ ጥረት ተደርጓል፡፡

የኤርትራ ጦርነት ጊዜ በኤላ በረድ የነበረውን የካሲያኒ ዴናኒይ የወይን እርሻና የኢላበረድ ወይን ፋብሪካን ሻቢያ ያጠፋውንና ያቃጠለውን እርሻም እንዲያንሰራራ ፋብሪካውም መልሶ ተቋቋሞ የወይኑም፣ የቲማቲም ድልህ ፋብሪካውም እንዲሠራ የከብት እርባታውም ጥጆች ከካናዳ ድረስ በማምጣት እንደገና ወተትና አይብ እንዲያመርት በማድረግ ሰው ሰርቶ እንዲያድርና ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራ ዕማማኮ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡

በዚህ በአፍላ ጦርነት ወቅት ደቀመሐሪ የነበረውን የብስኩት ፋብሪካ ሻቢያ አቃጥሎትና አበላሽቶት የነበረውን ቤቱን በማደስ፣ መሣሪያውን፣ በመተካት ሰዎች ሠርተው በልተው የሚያድሩበት እንዲሆን ለማድረግ ብዙ ተደክሟል፡፡

በኤርትራ የሚኖሩ የአፋር ተወላጆች በዳህላቅ አካባቢ በአሳ ማጥመድ ሥራ እንዲራመድ በተለይ ዘመናዊ የአሳ ማስገር ሥራ እንዲሻሻል ከሉተራን ዓለም-አቀፍ ፌዴሬሽን ከዴንማርክ ቅርንጫፍ ጋር በመተባበር ዘመናዊ አነስተኛ አሣ ማስገሪያ ጀልባዎችን መሥራት እንዲማሩ በናኩራ ትምህርት ቤት እንዲሠራ ከወዳጄ ከአቶ ካሣ ገብሬና በኤርትራ የእማማኮ ተወካይ ከነበረው ከመቶ አለቃ ብርሃኑ ጋር ለዚህ ሁሉ የወረዳው አስተዳዳሪ ሆኖ ይሠራ ከነበረው ከአቶ ጠሀ ጋር ብዙ ልማት በናኩራ ተሰርቷል፡፡

ከረን አካባቢ ጣሊያኖች ሠርተውት የነበረውን ግድብ አሸዋና ድንጋይ ሞልቶት የነበረውን አሸዋውን በመጥረግ ግድቡን ሥራ ላይ በማዋል አትክልትና ፍራፍሬ እንዲመረት ተደርጓል፡፡ በምፅዋ ጦርነት የወደመውን ትምህርት ቤት መልሶ በመሥራት የከረንን የምድር ባቡር ጣቢያና ሆስፒታሉን በማደስ ከረን እንደገና ተመልሳ ነፍስ እንድትዘራ ተደርጓል፡፡

በዚያን ወቅት እህል ሜዳ ላይ ይቀመጥ ስለነበረ ለወደፊቱ ደምበኛ መጋዘን መሥራት ትኩረት ተሰጥቶት ነበር፡፡ ይህም የእህል ክምችት በ10 ክፍላተ ሀገራት ቢሆንም ለጊዜው ዕማማኮ ማከማቻ በሠራባቸው በአሰብና በምጽዋ ወደቦች፣ በድሬዳዋ፣ በጎንደር፣ በደሴ፣ በኮምቦልቻና በናዝሬት ብቻ ነበር፡፡

በመጋዘን በኩል ለመጠባበቂያ ክምችት የራሱ መጋዘን ስላልነበረው በእህል ሰብል ገበያ ድርጅት ለማስቀመጥም በአንድ ቶን 33 ብር ያስከፍል ስለነበር አብዛኛው ክምችት የሚቀመጠው በእማማኮ መጋዘን ነበር፡፡

የማከማቻ መጋዘን ያላቸው እማማኮና ግብርና ሚኒስቴር በተለይ ኤፒድ ከእማማኮ ጋር ከድርቁ ጋር በተያያዘ የመልሶ ማቋቋም ሥራ በጣምራ ይሠሩበት በነበረበት ጊዜ ዘርና ማዳበሪያ እንዲሁም እህል ማከማቻ መጋዘኖች ማሠሪያ የእርዳታ ገንዘብ ለድርቁ ተገኝቶ በነበረው ስለተሠራ በተለይ ዶ/ር ሰለሞን በኩረ (ለተወሰነ ጊዜ) የስዊድን ተወላጅ አማካሪዎች ፕሮፌሰር አይዛክሰንና ረዳታቸው ሚ/ር ሆኖበርግ (በኋላ የስዊድን አምሳደር ሆነው በኢትዮጵያ ያገለገሉት) ባደረጉት ጥረት የተሰሩ መጋዘኖች ስለነበረ እማማኮ፣ እህል ሰብል ገበያና ግብርና ክምችት የመያዣ መጋዘኖች ነበሩአቸው፡፡ ከዚህም መሐል እማማኮ 3.3 ሚሊዮን ኩንታል የሚይዙ መጋዘኖች፣ እህል ሰብል ገበያ 6.3፣ ሚሊዮን ኩንታል፣ እማማኮና ለዕርዳታ ያሰሯቸው የቆርቆሮ መጋዘኖች ይዞታ ሲቀነስ 5.7 ሚሊዮን ኩንታል ግብርና 2.05 ሚሊዮን ኩንታል ነው፡፡

የእህል ክምችት ድርጅት በእማማኮ ሥር ሆኖ የኮሚቴ አባላት ከእማማኮ፣ ከግብርና ምኒስትርና ከገንዘብ ምኒስትር ተወጣጥተው ተደራጀ፡፡ የሙያ እገዛ እንዲያደርጉ የእማማኮ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የፕላን አገልግሎት ኃላፊ፣ የእርሻ ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን ሥራ አስኪያጅ የብሔራዊ አስቸኳይ ጊዜ የመጠባበቂያ እህል ክምችት ሥራ አስኪያጅና የዓለም የምግብ ፕሮግራም ተጠሪ ያሉበት ነው፡፡

የእህል ክምችቱን በማዘዋወርና በመለዋወጥ በኩል ከእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ዕማማኮ ከአሰገድ ጋር በቅርብ ይሠራል፡፡ ለእርዳታ የሚሰጠውን በብድር በመስጠት አሮጌውን እህል በአዲስ ለመተካት ተሞክሯል፡፡ ከእህል ሰብል ገበያ ድርጅት ጋርም በማበደር የመለዋወጥ ተግባር ተፈጽሟል፡፡ ቢሆንም አሠራሩ በአብዛኛውን በበጐ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እንጂ የየድርጅቶቹ የሥራ ኃላፊነትና ድርሻ ተደርጎ ስላልተወሰደ አልፎ አልፎ ሥራው መጓተቱ አልቀረም፡፡ በተለይ የክምችቱ መጠን እየጨመረ ሲሄድ ወጪና ጉልበት ስለሚጠይቅ ችግሩ እየተባባሰ መሄዱ አልቀረም፡፡

## የእህል ሰብል ገበያ ኮርፖሬሽን

የእህል ሰብል ገበያ ድርጅት በ1969 ዓ.ም. ሲቋቋም ከዓላማዎቹ አንዱ ለችግር ጊዜ የሚሆን የመጠባበቂያ እህል እንደሚይዝ ይገልጣል። ሆኖም ይህ የመጠባበቂያ ክምችት ትኩረት ተሰጥቶት መጠኑና ዓይነቱ ታውቆና ተለይቶ አልተከማቸም።

ከዚህም የተነሳ ክምችት በመያዝ ለሚደርስበት ተጨማሪ ወጪ የሚያካክስበት ሁኔታም አልተገለጸም። በዚህ ሁኔታ ድርጅቱ ትኩረት ሰጥቶ የተንቀሳቀሰው ለሸማቹ እህል በማቅረብ ገበያውን ለማረጋጋት የሚያስችል የንግድ ሥራ ላይ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ አሳሳቢ የምግብ እጥረት ሲደርስ እገዛ ማድረጉ አልቀረም። በ1976/77 ዓ.ም. በደረሰው ድርቅ የተከሰተውን ረሃብ ለመቋቋም በተደረገው ጥረት ከለጋሾቹ ቃል የተገባለት እህል አገር እስኪገባ ድረስ 80,000 ቶን እህል በማበደር ጠቃሚ ድጋፍ አድርጓል።

የእሰገድ ክምችት ከፍ ሲል 670,000 ቶን፣ ዝቅ ሲል ደግሞ 498,000 እንደነበረ የ1979 ከመኸር በፊት የነበረው ክምችትና በ1980 መጋዘኖች ያሉት በትርፍ አምራች አውራጃዎች ስለሆነ ለብሔራዊው መጠባበቂያ የምግብ ክምችት አገልግሎት አመቺ አይደለም።

ስለዚህ ከአቅምና ከፍላጎት ጋር የተዛመደ አመርቂ የምግብ ክምችት እንዲኖረን የምግቦቹን አይነት ዝርዝር በጥናት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለክምችቱ ተግባራዊነት ከዕርዳታ ብቻ ሳይሆን ከመንግሥትም በጀት መመደብና የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ሃላፊነታቸው ተገልጾ በሕግ እንዲያውቁት በማድረግ የሙያ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች እንዲመደቡ ያስፈልጋል።

በምግብ ዕርዳታ በኩል አቅም ያለው ሁሉ ሠርቶ ምግብም ሆነ ገንዘብ እንዲከፈለው እንጂ ምግብ በነፃ እንዳይሰጥ ቀደም ብሎ የተወሰነ ቢሆንም በሚገባ ተግባራዊ እየሆነ አይደለም። ስለዚህ ሕፃናት አረጋውያንና አካለ ጎደሎ ሆነው መሥራት ከማይችሉት በስተቀር ለሌሎች ምግብ በነፃ እንዳይሰጥ መደረጉ በተግባር መረጋገጥ አለበት።

## የማስተባበር ተግባር

በአገር አቀፍ ደረጃ ያለው አማካሪ ጉባዔ በጥሩ ሁኔታ ቢሠራም አልፎ አልፎ የክፍለ ሀገር ባለሥልጣናትና የአውራጃ ኃላፊዎች ከተሰጠው መመሪያ ውጭ ጣልቃ በመግባት የዕማማኮን ሠራተኞች ውጥረት ውስጥ ይከቷቸው ነበር።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የሚያስተባብረው ክርስቲያን የእርዳታና የልማት ሥራ ድርጅት በማቋቋም በኩል ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። የረሃቡ ችግር በአስር ጠቅላይ ግዛት ተስፋፍቶ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግን በመገናኛ ብዙሃን ችግር ወደ ሰሙበት ወሎና ትግሬ ብቻ እየሄዱ ስለነበረ በየሳምንቱ አንዴ

የመመካከሪያ ስብሰባ ኮሚሽነሩ ይጠራ ስለነበረ እዚያ ስብሰባ ላይ ችግሩ ስለተነገረ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በየወሩ የሚወያዩበትና ሥራቸውን የሚያስተባብሩበት መድረክ እንዲያቋቁም ስምምነት ላይ ተደረሰና ኮሚሽነሩም ጭምር የሚገኝበት የመያዶች መድረክ ተፈጠረ፡፡ ሲጀመር አብዛኞቹ የእምነት ነክ ድርጅቶች ስለነበሩ የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት (Christian Relief and Development Association) ይባል ነበር፡፡ አሁንም የሚጠራው በዚሁ ስሙ ነው፡፡

**የዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ከተባባሪ ድርጅቶች ጋር የሠራው የመልሶ ማቋቋም ተግባር**

የአገራችን መሠረታዊ ችግር በልማት ያለመጎልበት መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ዝናብ ባጠረ ቁጥረ ረሃብ ይከሰታል፡፡ ገበሬውም ሆነ አርብቶ አደሩ እኩል ሸማችና እርዳታ ፈላጊ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው የመልሶ ማቋቋም እርምጃ የእርሻ በሬ ወይም የእጅ መሣሪያ መስጠት ነበር፡፡ በድርቁ የተጎዳው የወሎ ክፍለ ሀገር 344,393 አባ ወራዎች የሚያርሱት 172,196 ሄክታር መሬት ነበራቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ጥማድ በሬ ለመስጠት አቅም ስላልነበረ አቀናጅተው እንዲያርሱ ለሁለት ቤተሰብ አንድ በሬ ለመስጠት ታቅዶ የሚፈለገውን 106,861 የእርሻ በሬዎች ለመግዛት የሚያስፈልገው 37,401,550 ብር ነበር፡፡ ለሚታረሰውም መሬት የሚያስፈልገው 39,596.53 ኩንታል ዘርም ለሕዝብ ታደለ፡፡

በ1978 ዓ.ም የሚያስፈልገው ዕርዳታ ለእህል ነበር፡፡ ከዚህም ውስጥ 68.5 ሚሊዮኑ ለእህል ነበር፡፡ በ1980 ዓ.ም ለልማት የተገኘው የእርዳታ ገንዘብ ሃምሳ ሚሊዮን ሲሆን 60 ከመቶ ከመያዶች፣37 ከመቶ ከመንግሥታትና 3 ከመቶ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ነበር፡፡ በ1978 ዓ.ም. ከእለት ዕርዳታ የተገኘው የገንዘብ መጠን የዚሁ አሥር እጥፍ ነበር፡፡

ለምሳሌ ያህል በ1976/77 እና በ1977/78 የተገኘው አጠቃላይ ዕርዳታ 1,525,899,310 ብር ነበር ከዚህ መሓል በመንግሥት በኩል 584,412,542 ብር ሲገኝ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል የተገኘው ዕርዳታ 941,486,768 ብር ሲሆን ከመንግስት ከተሰጠው ብር 35,774,226 ብልጫ ነበረው፡፡ ለዘላቂ ልማት የሚያገለግለው ዕርዳታ ለዕለት ደራሽ የዋለውን የዕርዳታ መጠን ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በ1976/78 በዕርዳታ ማስተባበሪያና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል በዓይነት የተገኘው ዕርዳታና የገንዘብ ተመኑ፡-

### *ሠንጠረዥ፣ በዕማማኮና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል የተሠራጨ ዕርዳታ*

| የዕርዳታው ዓይነት | መለኪያ | በመንግሥት በኩል የተሰጠ ዕርዳታ | | መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል የተሰጠ ዕርዳታ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የቁጥሩመጠን | በብር | መጠን | በብር ሲተመን |
| እህል | በኩንታል | 9,311,780 | 383,719,480 | 8,585,550 | 452,160,492 |
| አልሚ ምግብ | በኩንታል | 598,800 | 62,770,011 | 2,089,900 | 270,280,343 |
| መኪና (የጭነት) | በቁጥር | 1,177 | 61,230,210 | 598 | 46,341,319 |
| የመኪና ተሳቢ | » | 294 | 8,554,668 | 262 | 6,348,016 |
| ተሽከርካሪ | » | 99 | 1,945,819 | 871 | 18,568,898 |
| መለዋወጫ ዕቃ | » | | 8,985,080 | - | 24,046,862 |
| የሕክምና መሣሪያ | » | | 18,332,457 | - | 17,479,722 |
| አልባሳት | » | | 6,545,489 | - | 36,927,879 |
| የእርሻ መሣሪያዎች | » | | 114,316,863 | - | 22,414,427 |
| የቤት ቁሳቁስ | » | | 4,976,420 | - | 12,906,304 |
| የግንባታ መሣሪያዎች | » | | 11,429,437 | - | 20,439,522 |
| ሌሎች | » | | 1,606,608 | - | 13,572,984 |
| ድምር | | | **584,412,542** | | **941,486,768** |

*ከሰንጠረዡ እንደሚታየው ለቋሚ ልማት የዋለው ለጤና መሣሪያ በድምሩ ብር 25,812,179 የጤና አገልግሎት ለማሻሻል የበኩሉን አስተዋጽዖ አድርጓል:: ለጭነት መኪናና ለተሳቢ ለመለዋወጫ ዕቃዎች የተገኘው ዕርዳታ ብር 160,703,110 በትራንስፖርት በኩል ያለውን አቅም በመገንባት ትልቅ ድጋፍ ነበር:: ቢሆንም አነስተኛ የመኪና ብዛት ለነበረው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለመለዋወጫ ለዕማማኮ ከተሰጠው 15,101,782 ብር መብለጡ ያስተዛዝባል:: በተጨማሪም ለአነስተኛ ተሽከርካሪዎች በመያድ በኩል የተሰጠው ዕርዳታ ለመንግሥት ከተሰጠው ብር 16,623,079 መብለጡ ሌላው አጠያያቂ ሁኔታ ነው::*

*በዕርሻ መሣሪያዎች በኩል ብር 136,731,290 የሚገመት መሣሪያ መገኘቱ በእርሻ ልማት በኩል የሚደረገውን ጥረት ያጎለብት ነበር:: ስለዚህ ምንም እንኳን ለዘላቂ ልማት የነበረው ድጋፍ ከጊዜያዊ ዕርዳታ ሲተያይ አነስተኛ ቢሆንም የበኩሉን የልማት አቅም ግንባታ አድርጓል::*

### የመልሶ ማቋቋምና ራስን መቻል እንቅስቃሴዎች

*ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የእርሻ ልማት ሁኔታ በአይነትና በመጠን ተሻሽሎ በምግብ ራስ ካልተቻለ የማንወጣው አዙሪት ውስጥ እንገባለን:: በወቅቱ የኢትዮጵያ የነበረችው የኤርትራ፣ የትግራይ፣ የወሎ፣ የጎንደርና የሰሜን ሸዋ ደን የተራቆተ ስለነበረ አፈሩ በሚያስደነግጥ መጠን እየታጠበ ነበር::*

*በወቅቱ ከዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት ጋር የተደረገው ጥናት የሚከተለውን ሁኔታ ያሳያል፡- ከሕዝባችን 85 በመቶ በተራራማዎች አካባቢ መኖሩን፣95 በመቶ የእርሻ መሬትና ከከብት ሃብታችን 2/3ኛው የሚገኘው በእዚሁ አካባቢ መሆኑንና ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴአችን 90 በመቶው ያለውን ደጋፊ ክፍል መሆኑ ነው፡፡ ከደጋፊው 270,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ግማሹ አፈሩ የታጠበ ከዚህም ውስጥ 20,000 ካሬ ኪሎ ሜትሩ ያህሉ እህል ማብቀል የማይችል ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ 10,000,000 ገበሬዎች የሚያርሱት መሬት አልነበራቸውም፡፡ ከጠቅላላው ደጋ መሬት በዓመት 1,900,000,000 ቶን ያህል አፈር እየታጠበ ሲሄድ ከታረሰው ክፍል ደግሞ 100,000 ቶን አፈር በዓመት ተጠርጎ ይሄዳል፡፡ ይህን ሁኔታ የሚያባብሰው ደግሞ በፍጥነት እየጨመረ የሚሄደው የሕዝብ ቁጥር ነው፡፡*

*በመልሶ ማቋቋም መርሃ ግብር በስፋት የተሠራው ለገበሬው የሠፈራ ሥራ ለአርብቶ አደሩ ደግሞ ከብቱን የሚያግጠው መኖና ለከብት መጠጥ ያለውን ውሃ ማመቻቸት ነበር፡፡*

### ለአርብቶ አደሩ የመልሶ መቋቋም ተግባር

*አርብቶ አደሩ ከብቱ ሲያልቅ የርቢ ከብት መስጠትና የእንስሳት ጤንነት እንዲጠበቅ ክትባትና ሕክምና ማካሄድ ነው፡፡ በተለይ በሰሜን ምሥራቅ፣ በደቡብ በቦረና በደቡብ ምሥራቅ በኦጋዴን የነበሩት የከብት ዕርባታ ፕሮጀክቶችን የሚያግዝ ዕርዳታ ተሰብስቦ የኑሮ ዋስትና እንዲኖራቸው ጥረት ተደርጓል፡፡ በአሊደጌ (አፋር ውስጥ) የመስኖ ግጦሽ ሙከራ፣ በአሬሮና በተልተሎ የውሃ ግድብ በአመቺ ቦታዎች በመሥራት የነበሩ ጅምሮች አሁንም መቀጠል አለባቸው፡፡*

*በገዋኔ፣ በዱብቲና በአሳይታ አርብቶ አደሩን ለማስፈር ጥረት ተደርጓል፡፡ በኦጋዴን ከጎዴ አንስቶ በቀላፎ፣ በሙስታሂልና በብሩኩል ሰፋፊ የመስኖ እርሻዎች እየተከናወኑ ነበር፡፡*

### የአርሶ አደሩ የመልሶ ማቋቋም ሥራና ሠፈራ

*በዓለም ባንክ ዕርዳታ ኮሚሽኑ ባደረገው ጥናት መሠረት ከዓለም ባንክ በተገኘ 10,000,000 ዶላር የሲሪንቃን ተፋሰስ ለማልማት በ1970 ዓ.ም. ሥራ ተጀመረ፡፡ የፕሮጀክቱ ስፋት 370 ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን በውስጡ ያለውም 450,000 ሕዝብ በ33 ገበሬ ማኅበራት የተደራጀ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ዓላማ አካባቢውን ለመለወጥና የአፈሩንም ለምነት ለማደስና የአካባቢውን ደንና ቁጥቋጦ መልሶ ለማልበስ ነበር፡፡*

*የልማቱ ሥራ እቅድ 1,183,834 ዛፎች ለመትከል፣ 18,595 ቦረቦሮችን ለመድፈን ፣ በሣር የተሸፈኑ የውሃ ቦዮችን ለመሥራት፣ ሦስት ግድቦችንና አምስት ኩሬዎችን ለመገንባት፣ ሁለት የውሃ አቅጣጫ መቀየሪያ ግድቦችን ለመገንባት፣ ሁለት የውሃ አቅጣጫ መቀየሪያ*

ግድቦች፣ 58 ከሎ ሜትር የመኪና የእርከን ሥራ፣ 432 ኪሎ ሜትር እርከን ፣35 ኪሎ ሜትር መንገድ ፣435.5 ሜትር የመስኖ ቦይ 2 ኪሎ ሜትር አፈር መጠበቂያ ግምብ ለወንዙ ለመሥራት የመሳሰለውን የያዘ ነበር፡፡

ሌላው የተፋሰስ ልማት በምዕራብ ጀርመን ዕርዳታ የተካሄደው የቆቦ አላማጣ ልማት አካል የሆነው የጎሊና ሆርማት ተፋሰስ ነው፡፡ ጎሊና ሆርማት ተፋሰስ ላይ 3,243 ኪሎ ሜትር የሚሆን በአፈር ጥበቃ ሥራ ተሠርቷል፡፡ 2,376,285 ዛፍ ተተክሏል፡፡ እንዲሁም 12 ባዮ ጋዝ፣ 38 የተሻሻሉ የገጠር ቤቶች ናሙና፣ 53 ኪሎ ሜትር መንገድና የወንዙን ፍሰት የሚለኩ ስድስት ሃይድሮ ሜትሮች ተተክለው ነበር፡፡ በተጨማሪም ለአካባቢው ገበሬ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥልጠና ሰጥተው ነበር፡፡

እነዚህን የመሠሉት ኘሮጀክቶች በቀጣይነት ቢሠሩና በሌሎች ሥፍራዎችም ቢደገሙ አስጊውን የአየር ንብረት ለውጥ መግታትና ማሻሻል እንደሚቻል አቀጣጫ አሳይተዋል፡፡

## የሠፈራ መርሃ ግብር

*የሠፈራ መርሃ ግብር በስፋት የተጀመረው በ1977 ዓ.ም የሠፈራ ባለሥልጣን በአዋጅ ከዕማማኮ ጋር ከተዋሃደ በኋላ ነው፡፡ መጀመሪያ በጅባትና ሜጫ አውራጃ ሀሮሌና በደሌ በሚባሉት ቀበሌዎች ሠፈራ በስፋት የተሠራ ሲሆን በ1977 ዓ.ም. ከወሎ 300,000 ሕዝብ ለማስፈር ተወስኖ እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡*

*ሠፈራው ሁለት ዓይነት ሲሆን አንዱ ስግሰጋ ነበር - ማለትም ባሉ ገበሬ ማኀበሮች ውስጥ ሰፋሪዎችን በትርፍ ቦታ መሰግሰግ ነበር፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ድንግሉ መሬት ላይ የሚደረገው ሰፋፊ ሠፈራ ነው፡፡*

### ሠንጠረዥ፣ የሰፋሪዎች መኖሪያዎች ክልልና የሰፈሩበት ክልል

| የክልሉ መገኛ | የሠፋሪዎች መኖሪያዎች ክልልና የሠፋሪዎች ቁጥር | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከፋ | ኢሉባቦር | ሸዋ | ወለጋ | ጎንደር | ጐጃም | ድምር |
| ወሎ | 44,334 | 72,226 | - | 220,636 | - | 29,820 | 367,016 |
| ሸዋ | 6,514 | 29,322 | 6,149 | 11,279 | - | 54,977 | 108,241 |
| ጐንደር | - | - | - | - | 6,387 | - | 6,387 |
| ትግራይ | 21,982 | 46,367 | - | 21,367 | - | - | 89,716 |
| ጐጃም | - | - | - | - | - | 16,425 | 16,425 |
| ድምር | 72,830 | 147,915 | 6,149 | 253,282 | 6,387 | 101,222 | 587,785 |

በ1977/78 ከወሎ 376,298 ሰዎች እንዲሰፍሩ ተደረገ፡፡ ይህም በወሎ አጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር 11.2 በመቶ መሆኑ ነው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ አብዛኛውን ሕዝብ የወሰደው መንገድ ካለበትና በቀላሉ ከሚደረሱ አውራጃዎች ነው፡፡

**ሠፋሪዎች በአውራጃ**

***ከእነዚህ ሠፋሪዎች ውስጥ 59 በመቶ የሚሆኑት የሰፈሩት ወለጋ፣ 19 በመቶ ኢሉባቡር፣ 14 በመቶ ከፋ እና 8 ከመቶ ጎጃም ነው።***

**ሠንጠረዥ፣ የስግሰጋ ሠፈራ በክልል**

| ክልል | የገበሬ ማኅበራት ቁጥር | አባወራ | | የቤተሰብ አባል | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | |
| ወለጋ | 724 | 267 | 28 | 57 | 887 | 84,613 |
| ኢሉባቦር | 428 | 23,464 | 3,872 | 25,614 | 37,172 | 90,122 |
| ከፋ | 155 | 13,828 | 2,685 | 23,479 | 36,827 | 53,340 |
| ድምር | **1,325** | **70,577** | | **157,500** | | **228,077** |

- ***ሠፋሪዎችን ያቋቋመ ክልል 62.4 በመቶ ከሸዋ፣ 18.4 በመቶ ከትግራይ፣***

- ***የሠፈረበት ክልል 43.1 በመቶ ኢሉባቡር፣ 25.2 በመቶ ጎጃም፣ 17.2 በመቶ ከፋ፣ 12.4 ጎንደርና ሸዋ***

- ***በትልልቅ ሠፈራ መርሃ ግብር ሞዴል እያንዳንዱ ሰፈራ ጣቢያ አምስት መቶ ቤተሰቦችን የሚያካትት ሲሆን የመሬት ድልደላውም እንደሚከተለው ነው፡-***

   1. *1,000 ሄክታር በጋራ የሚታረስ*
   2. *200 ሄክታር ለደንና ለከብት ግጦሽ*
   3. *50 ሄክታር ለቤት መሥሪያና የጓሮ አትክልት*

***በዚህ መሠረት አንድ ሠፈራ ጣቢያ 1,250 ሄክታር መሬት ይዞታ ያለው ነበር። ሠፈራው አገልግሎቶችን አካቶ አዋጪ እንዲሆን አምስት ሠፈራ ጣቢያዎች በአንድነት መካተት አለባቸው። የማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ የጤናና የትምህርት ተቋማት ይመሰረታሉ። የውሃ አገልግሎት ይሠራል። በተጨማሪም መንገድ፣ መጋዘን፣ ክሊኒክ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ የእጅ ሥራ፣ የጥገና፣ የኅብረት ሱቅና ጽሕፈት ቤቶችም ይገነባሉ።***

***የሠፈራ መርሃ ግብርን ለመፈጸም የሚያስፈልገው ወጪ ትራንስፖርትን ሳይጨምር እንኳን ከፍተኛ ነው። ለሰፈራ የወጣው ወጪ የግንባታ ሥራዎችን፣ የጤናና የትምህርት ሚኒስትሮችና የውሃ ኮሚሽን ያወጡትን ሳይጨምር ብር 564.4 ሚሊዮን ነበር።***

***የሕዝብ ማስፈር ሥራ በአፈጻጸም ስህተት ምክንያት ብዙ ወቀሳ ያስከተለና እርዳታ ሰጭዎችም እምብዛም ያልደገፉት ሥራ ነበር። በመሠረቱ በጥናትና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሠፈራ እንዲከናወን***

ከተጣበበውና ብጥስጣሽ ከሆነው የመሬት ይዞታ አካባቢ ወጥቶ ሰፋ ያለ እርሻ ከሚገኝበት ሰዎች እንዲሄዱ ዕርዳታ ሰጪዎች ቢደግፉም አሰራሩን አልወደዱትም ነበር፡፡

ዕማማኮ ከሠፋሪው መነሻና መድረሻ ቦታ ላይ ጥናት አካሂዶ የሚከተለው ድምዳሜ ላይ ደርሶ ነበር፡፡

1. መስፈር የሚፈልጉ ቢኖሩም የሰፋሪ ምልመላ በፈቃደኝነት አለመሆኑ፣ ለወረዳው የተመደበውን ኮታ ለመሙላት በግዴታ መሆኑ
2. ሠፋሪው የት እንደሚሄድ በሚገባ ሳይገለጽለት፣ ንብረቱን ለመሰብሰብና ዘመድ ለመሰናበት ጊዜ ሳይሰጠው ሠፈራ ጣቢያ ገብቶ እየተጠበቀ መቆየቱ
3. የሠፋሪ ምልመላ ምዝገባና የጉዞ ክንውኑም መልክ ያለው ስላልነበረ የቤተሰብ መለያየትና ልጆችና ወላጆች ተለያይተው ጠባቂ የሌላቸው ሕፃናት ሠፈራ ጣቢያ መገኘት
4. ከጉዞ በፊት ሰፋሪው እሚሰባሰብበት ጣቢያ የመጸዳጃ ሥፍራና፣ የሕክምና አገልግሎት አለመመቻቸት በፈጠረው ችግር በሽታና ሞት መከሰቱ በጉዞ ላይም የነበሩ ማረፊያ ጣቢያዎች የታመሙትና የሚጠቡትን ሕፃናትን ለማስተናገድ ዝግጅት አለመኖሩ
5. የሰፋሪው የወትሮ መኖሪያው አካባቢ ያለው አየር ንብረት ከሠፈረበት ልዩ በመሆኑ የተነሳ ሕመምተኛ መብዛቱ
6. የሰፈሩበት ቦታ በቂ የእርሻ መሬት አለመኖርና የመጠጥ ውሃ ባለመኖሩ ቤት አፍርሶ ሌላ ቦታ መጓጓዝ መኖሩ
7. ለእርሻ የሚያስፈልገው ዘርና መሣሪያ በወቅቱ ባለመቅረቡ የእርሻ ጊዜ መተጓጓሉ
8. የግል ይዞታ የለመዱ ገበሬዎች የኔ ነው የሚሉት ይዞታ አለመኖሩና ለጓሮ አትክልት የሚሰጠውም ተለይቶ አለመታወቁ፤ ግድየለሽነት ስሜት መፍጠሩና ለማምረት ያለው ፍላጎት መጥፋቱ... የመሳሰሉት ይገኝበታል፡፡

ከሰፈራ ቦታ ጠፍተው የሄዱትም ተጠይቀው የሰጡት መልስ የሚከተለው ነው፡-

1. 30 ከመቶ የሚሆነው ሠፋሪ ሠፈራ የተላከው በግድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ቢሆንም በተራ ቁጥር ሦስት ካለው ጋር ሲተያይ አነስተኛ ይመስላል፡፡
2. ከሠፈሩበት ክልል ቀድሞ ወደነበሩበት ለጉብኝት እንኳን መሄድ አለመፍቀድና፣ ሠፈራው ባይስማማቸው ቀድሞ ወደነበሩበት ለመመለስ አለመቻሉ
3. 75 በመቶው ከቤተሰባቸው በመለየታቸው መሆኑን ይገልፃሉ ፡፡ (ይኼ ትንሽ የተጋነነ ይመስላል)
4. 67 በመቶው የተገባላቸው ቃል አለመፈጸሙን ገልጸዋል

5. *የቤተ አምልኮ አለመኖርና የለመዱት የባሕል ወጎችና የኃይማኖት በአላት መዘንጋት*
6. *ሠፋሪዎች ስለሚሄዱበት አካባቢ መረጃ አለማግኘትና ካሉት የሠፈራ ጣቢያዎች መሐል የሚፈልጉትን መምረጥ አለመቻላቸው*

*ከአሁን ቀደም ሰዎች በፍላጎታቸው ካሉበት ወደ ሌላ እየሄዱ ደን መንጥረው ጎጆ ሠርተው በራሳቸው ይሰፍሩ ነበር፡፡ አሁን ግን ከፍተኛ ወጪ ወጥቶ በ1977 ብር 89,344,586፣ በ1978 ደግሞ ብር 106,080,499 ወጥቶ በምግብ፣ በቁሳቁስ፣ በርሻ መሣሪያ ታግዞም ሠፈራን እየለቀቀ ይሄዳል፡፡ በ1977 ከነበረው ሰፋሪ በ1981 ያለው ሰፋሪ ቁጥር በ100,000 ቀንሷል፡፡ ለዝርዝሩ የሚከተለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ፡፡*

**ሠንጠረዥ፣ ብዙ ሕዝብ የሰፈረበት አካባቢ**

| *የሰፋሪዎች መገኛ* | *ዓመታት* | | | | | *ምርመራ* |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ***1977*** | ***1978*** | ***1979*** | ***1980*** | ***1981*** | |
| *ወለጋ* | 246,268 | 252,714 | 128,717 | 128,311 | 124,884 | **1) 1977** *የሰፋሪዎች መገኛ*<br>*ወሎ 60%*<br>*ሸዋ 19%*<br>*ትግራይ 17%*<br>*ጐጃም 3%*<br>*ጐንደር 1%*<br>*2) በ1979 ተሰግስገው የሰፈሩ ወለጋና ሸዋን ሳይጨምር*<br>*3) 1980 ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ*<br>*4) 1981 ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ* |
| *ኢሉባቦር* | 119,078 | 144,943 | 135,486 | 131,866 | 111,763 | |
| *ከፋ* | 48,229 | 56,958 | 53,340 | 56,247 | 38,958 | |
| *ጐጃም* | 67,158 | 56,644 | 73,660 | 80,266 | 77,816 | |
| *ሸዋ* | 6,149 | | | | | |
| *ጐንደር* | 6,387 | 4,831 | 4,710 | 2,696 | 6,844 | |
| *ድምር* | 493,269 | 516,090 | 395,913 | 399,380 | 360,265 | |
| | | | | | | |

**ዕማማኮ ያስጠናው የወሎና ትግራይ የኘሮጀክት ጥናቶች ግምገማ**

*ዕማማኮ ከዓለም ባንክ ባገኘው ዕርዳታ በተደረገው የኘሮጀክቶች ግምገማ ወቅት ቀደም ሲል የተጠኑ ጥናቶችን በመመርመርና ተጨማሪ የኘ ሮጀክት ሃሳቦችን በማቅረብ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲሠሩ የቀረቡት የሚከተሉት ናቸው፡-*

1. *የሥሪንቃ ተፋሰስ ጥበቃ*

2. *የማዕከላዊ ትግራይ ልማት የመሬትና የውሃ ሃብት ጥበቃ ጥናት በእንግሊዝ ዕርዳታ የሀንቲንግስ አማካሪ ቡድን* (Huntings Consultants) *ያጠናው*

3. *የታችኛው አዲያቦ ኘሮጀክት በትግራይ ከደጋው 12,000 ገበሬዎች ለማስፈር በዓለም ባንክ እርዳታ የተደረገ ጥናት*

4. *የወሎና የትግራይ ውሃ ልማት መሪ ዕቅድ*

5. *የወሎና የትግራይ የገጠር መንገዶች ሥራ መሪ እቅድ*

**ሌሎች የአፈርና ውሃ ጥበቃና ልማት እቅዶች**

*ከሌሎች ጥናቶች መሐል በሥራ ቢውሉ በምግብ ራስን ለመቻል ያግዛሉ ተብለው ዕማማኮ ከሚከታተላቸው መሃል፣*

1. *በስግሪያ የተጠናው የዴዴሳ ልማትና አፈር ጥበቃ 500,000 ሄክታር የሚሸፍን፣*

2. *የጎዴ መስኖ እርሻ ቀደም ሲል በጃንሆይ ጊዜ በፈረንሳዩ ኩባንያ በሲኤም የተጠና፣*

3. *በአዋሽ ሸለቆ በግል ኩባንያዎች ይታረሱ የነበሩ መሬቶች ሲወረሱ በግብርና ሚኒስቴር ለሚታረሰውና አፋር አርብቶ አደር እንዲሠፍርበት የተደረገው ልማት፣*

4. *በፓዊ (መተከል) የተጀመሩት የሠፈራና የልማት ሥራዎች ይገኙበታል::*

## የዕርዳታና የመልሶ ማቋቋም ሥራ ተዛምዶ

የገጠር መሠረተ ልማት ቢዘረጋ፣ መብራትና ውሃ በገጠር እንዲገኝ ቢደረግ፣ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ በሚገባ ቢደራጅና ዘመናዊ የምርት ስልትን ቢከተል ዝናብ ባጠረ ቁጥር ረሃብን አያስከትልም ነበር በሚል መነሻ የዕርዳታ ማስተባበሪያን ተቋም ለማሻሻል ጥናት ተደርጓል:: ከዚህም የተነሳ አግባብ ያላቸው መሥሪያ ቤቶች ከኘላን ሚኒስቴር፣ ከዕማማኮ፣ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከውሃ ኮሚሽን፣ ከደን ልማት ባለሥልጣን የተውጣጣ ቡድን በእኔ መሪነት ሕንድና ቻይናን እንዲጎበኝ ታቅዶ ነበር:: በዚህ መሠረት ሕንድ የሚሄደውን ቡድን መርቼ ሄደን ከመንግሥት ባለሥልጣናት፣ በመስክ ከሚሠሩ በሳል ባለሙያዎችና ከገበሬዎች ጋር ውይይት አካሂደን መጥተናል:: ቻይናም እኔ በሌላ አስቸካይ ሥራ ምክንያት ባልሄድም ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ቻይና ሄደው ተመሳሳይ ተግባር ፈጽመው ከመጡ በኋላ ለመንግሥት ሪፖርት ቀርቧል:: በሪፖርቱም መሠረት ምኒስትሮች፣ ባለሙያዎች፣ መያዶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚገኙበት ስብሰባ ተደርጎ ከቻይናና ከሕንድ ምኒስትሮችና እንደ ዶ/ር ሰዋሚታን ያሉ ታዋቂ ባለሙያዎችም ሃሳብ ያቀረቡበት ውይይት ተደርጓል::

በስብሰባው ውሳኔ መሠረትም የተባበሩት መንግሥታት የልማት ኘሮግራም አንድ በሳል ሕንዳዊ ባለሙያ በማቅረብ ደምብና ረቂቅ ሕግ እንዲያዘጋጅ ሆነ:: ከዚህ በኋላ የመንግሥት ለውጥ ሆኖ ኢሕአድግ ሲመጣ የዚህን ረቂቅ የተወሰኑትን በመመሪያ መልክ አውጥቶ የቀድሞውን አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፫/፲፱፻፸ ዓ.ም. ለውጦ ቀድሞ የነበሩትን ኃላፊነቶች ቀንሶ የአደጋ መላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንን አቋቁሞ ኮሚሽነሩ ከዘጠኙ አካላት አንዱ ሆኖ መንግሥት የሚሾመው ሊቀመንበር ያለው የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ብሔራዊ ኮሚቴ መቋቋሙን በአዋጅ ቁጥር ፩፻፸፫/፲፱፻፹፯ ዓ.ም ዓ.ም አሻሽሎት እስካሁን እየተሠራበት ነው::

## ማጠቃለያ

የእርዳታ ማስተባበሪያ ሥራዬን በጀመርኩበት ዓመት የዓለም የምግብ ጉባዔ ሮም ላይ ተጠርቶ የድርቅና የረሃብ አሳሳቢነትን በሳህልና በኢትዮጵያ የደረሰው የሰውና የከብት ዕልቂትን ግምት ውስጥ በማስገባት የዓለም የምግብ ምክር ቤት የሚባል አዲስ ድርጅት እንዲቋቋም ውሳኔ አሳለፈ:: በዚህ ጉባዔ ላይ በወቅቱ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሄኒሪ ኪሲንገር ከአሥር ዓመት በኋላ አንድም ልጅ እንደራበው ወደ መኝታው አይሄድም ብለው ነበር:: ዛሬ ከሦስት አሠርት ዓመታት በኋላ ልጆች እንደተራቡ ወደ መኝታቸው መሔድ ብቻ ሳይሆን በረሃብ የሚሞቱት ቁጥር ጨምሯል::

ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ለመቻል በግድ በዝናብ ላይ ብቻ ከሚተማመን እርሻ መላቀቅ አለብን፤ በማለት በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ

መንግሥት የተደረጉ ከአሜሪካ ቢሮ ኦፍ ሬክላማሽን ባለሙያዎችና በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የተጠናው የአባይ ተፋሰስ፣ የግቤ፣ የኦሞና የዋቢ ሸበሌ ጥናቶች ሥራ ላይ አልዋሉም:: የተጀመሩ የልማት ሥራዎችም ሲቆሙ ሌሎች ደግሞ ሳይጀመሩ በእቅድ ብቻ ቀሩ:: እንደባለሙያዎች አስተያየት በመስኖ ሊለማ ከሚችለው መሬት 5% ብቻ ሲሆን የለማው ከውሃ ልናመነጭ ከምንችለው የመብራት ኃይል ደግሞ 2% ብቻ ነበር ማምረት የተቻለው:: ይህን የተፈጥሮ ሀብታችንን ተግባራዊ ለማድረግ የዓለም ባንክና ሌሎች አበዳሪ ድርጅቶች በተለይ በዓባይ ተፋሰስ የሚጠቀሙ አገሮችን ይጎዳል በሚል ሰበብ ለመተባበር ዘገምተኛ ነበሩ:: ስለዚህ ዓባይን በጭልፋ አይቻልም:: የተባለውን አባባል ለውጡን አባይን በጭልፋ መቻሉን በገባር ወንዞቹ ላይ ባለን አቅም ሥራ በመጀመር በምግብ እራስን የመቻል ጉዞአችንን መጀመር አለብን::

ለዚህም መልካም ውጤት ሕዝቡ ባለሙያውና መንግሥት መደማመጥና መናበብ መቻል አለባቸው:: መንግሥት ሕዝብን ካላዳመጠ ለልማት የሚያመቹ የአስተዳደርና የሕግ ሥርዓቶች ካልተዘረጉና በሥራ ላይ ካልዋሉ ያሰብነው አይደርስም:: በየስብሰባው የሚነሱትን በጎ ሃሳቦችና ውሳኔዎችን ለመተግበር ጥሩ አስተዳደር፣ ግልፅነትና ለሕዝብ ተጠያቂነት በአስተማማኝ ሁኔታ ካልተረጋገጠ ከፍሬ ለመድረስ ያስቸግራል::

የአገራችን አንዱ ትልቅ ችግር የመንግሥት ለውጥ የመጣው በምርጫ ሳይሆን በኃይል ስለሆነ የተተኪው መንግሥት ትኩረት መቀመጫውን ለማደላደል ሲል ያለፈውን መንግሥት በመኮነን የራሱን ሥራ አጉልቶ ለማሳየት በሚያደርገው ጥረት ኃይሉን መጨረሱ ነው:: ከዚህም የተነሳ ቀድሞ የተሠራው በጎ ሥራ ላይ መገንባት የለም፤ የተጀመረውንም አይጨርስም:: እንዲያውም ከእነአካቴው የፊተኛው መንግሥት ላይ ያየውንና የኮነነውን ነውር መድገሙ ነው::

በ1966 ዕማማኮ ሲቋቋም የነበረው የፍትሃዊነትና የአስተማማኝ የመሬት ይዞታ ጉዳይ ዛሬም አልተፈታም፤ ዛሬም እያከራከረ ነው:: በእውነት በምግብ እራሳችንን ለመቻል ከፈለግን የተጠናውን ጥናት በመረጃ ላይ በተመረኰዘ ቅደም ተከተል መሥራት የተጀመሩና በሥራ ላይ የነበሩትን ደግሞ መጨረስና ውጤት እንዲያስገኙ ማድረግ የሁላችንም አገራዊ ግዴታና ኃላፊነት ነው::

# FSS Publications List

## FSS Periodical

*Medrek, now renamed BULLETIN* (Quarterly since 1998. English and Amharic)

## FSS Discussion Papers

No. 1 *Water Resource Development in Ethiopia: Issues of Sustainability and Participation*. Dessalegn Rahmato. June 1999
No. 2 *The City of Addis Ababa: Policy Options for the Governance and Management of a City with Multiple Identity*. Meheret Ayenew. December 1999
No. 3 *Listening to the Poor: A Study Based on Selected Rural and Urban Sites in Ethiopia*. Aklilu Kidanu and Dessalegn Rahmato. May 2000
No. 4 *Small-Scale Irrigation and Household Food Security. A Case Study from Central Ethiopia*. Fuad Adem. February 2001
No. 5 *Land Redistribution and Female-Headed Households.* By Yigremew Adal. November 2001
No. 6 *Environmental Impact of Development Policies in Peripheral Areas: The Case of Metekel, Northwest Ethiopia*. Wolde-Selassie Abbute. Forthcoming, 2001
No. 7 *The Environmental Impact of Small-scale Irrigation: A Case Study*. Fuad Adem. Forthcoming, 2001
No. 8 *Livelihood Insecurity Among Urban Households in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato and Aklilu Kidanu. October 2002
No. 9 *Rural Poverty in Ethiopia: Household Case Studies from North Shewa.* Yared Amare. December 2002
No.10 *Rural Lands in Ethiopia: Issues, Evidences and Policy Response.* Tesfaye Teklu. May 2003
No.11 *Resettlement in Ethiopia: The Tragedy of Population Relocation in the 1980s.* Dessalegn Rahmato.
June 2003
No.12 *Searching for Tenure Security? The Land System and New Policy Initiatives in Ethiopia.* Dessalegn Rahmato. August 2004.

## FSS Monograph Series

No. 1 *Survey of the Private Press in Ethiopia: 1991-1999*. Shimelis Bonsa. 2000
No. 2 *Environmental Change and State Policy in Ethiopia*: *Lessons from Past Experience*. Dessalegn Rahmato. 2001
No. 3 *Democratic Assistance to Post-Conflict Ethiopia: Impact and Limitations.* Dessalegn Rahmato and Meheret Ayenew. 2004

## Special Monograph Series

1. *Lord, Zega and Peasant: A Study of Property and Agrarian Relations in Rural Eastern Gojjam. Habtamu Mengistie. 2004*

## FSS Conference Proceedings

1. *Issues in Rural Development. Proceedings of the Inaugural Workshop of the Forum for Social Studies, 18 September 1998*. Edited by Zenebework Taddesse. 2000
2. *Development and Public Access to Information in Ethiopia*. Edited by Zenebework Tadesse. 2000
3. *Environment and Development in Ethiopia*. Edited by Zenebework Tadesse. 2001
4. *Food Security and Sustainable Livelihoods in Ethiopia*. Edited by Yared Amare. 2001
5. *Natural Resource Management in Ethiopia.* Edited by Alula Pankhurst. 2001
6. *Poverty and Poverty Policy in Ethiopia.* Special issue containing the papers of FSS' final conference on poverty held on 8 March 2002

## Consultation Papers on Poverty

No. 1 *The Social Dimensions of Poverty*. Papers by Minas Hiruy, Abebe Kebede, and Zenebework Tadesse. Edited by Meheret Ayenew. June 2001

No. 2 *NGOs and Poverty Reduction*. Papers by Fassil W. Mariam, Abowork Haile, Berhanu Geleto, and Jemal Ahmed. Edited by Meheret Ayenew. July 2001

No. 3 *Civil Society Groups and Poverty Reduction*. Papers by Abonesh H. Mariam, Zena Berhanu, and Zewdie Shitie. Edited by Meheret Ayenew. August 2001

No. 4 *Listening to the Poor.* Oral Presentation by Gizachew Haile, Senait Zenawi, Sisay Gessesse and Martha Tadesse. In Amharic. Edited by Meheret Ayenew. November 2001

No. 5 *The Private Sector and Poverty Reduction [Amharic]*. Papers by Teshome Kebede, Mullu Solomon and Hailemeskel Abebe. Edited by Meheret Ayenew, November 2001

No. 6 *Government, Donors and Poverty Reduction.* Papers by H.E. Ato Mekonnen Manyazewal, William James Smith and Jeroen Verheul. Edited by Meheret Ayenew, February 2002.

No. 7 *Poverty and Poverty Policy in Ethiopia.* Edited by Meheret Ayenew, 2002

## Books

1. *Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below*. Edited by Bahru Zewde and Siegfried Pausewang. Nordic African Institute, Uppsala and the Forum for Social Studies, Addis Ababa. 2002

## Special Publications

- *Thematic Briefings on Natural Resource Management. Enlarged Edition.* Edited by Alula Pankhurst. Produced jointly by the Forum for Social Studies and the University of Sussex. January 2001

## New Series

- **Gender Policy Dialogue Series**

No. 1 *Gender and Economic Policy.* Edited by Zenebework Tadesse. March 2003

No. 2 *Gender and Poverty (Amharic).* Edited by Zenebework Tadesse. March 2003
No. 3 *Gender and Social Development in Ethiopia.* (Forthcoming).
No. 4 *Gender Policy Dialogue in Oromiya Region.* Edited by Eshetu Bekele. September 2003
No. 6 *Gender Policy Dialogue in Southern Region.* Edited by Eshetu Bekele. December 2004.

- **Consultation Papers on Environment**

No. 1 *Environment and Environmental Change in Ethiopia*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. March 2003
No. 2 *Environment, Poverty and Gender.* Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. May 2003
No. 3 *Environmental Conflict*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. July 2003
No. 4 *Economic Development and its Environmental Impact*. Edited by Gedion Asfaw. Consultation Papers on Environment. August 2003
No. 5 *Government and Environmental Policy*. Consultation Papers on Environment. January 2004
No. 6 ***የግልና የጋራ ጥረት ለአካባቢ ሕይወት መሻሻል (የሰሜን ሸዋ ገበሬዎች ተሞክሮ)*** Consultation Papers on Environment. May 2004
No. 7 *Promotion of Indigenous Trees and Biodiversity Conservation.* Consultation Papers on Environment. June 2004

- **FSS Studies on Poverty**

No. 1 *Some Aspects of Poverty in Ethiopia: Three Selected Papers.* Papers by Dessalegn Rahmato, Meheret Ayenew and Aklilu Kidanu. Edited by Dessalegn Rahmato. March 2003.
No. 2 *Faces of Poverty: Life in Gäta, Wälo.* By Harald Aspen. June 2003.
No. 3 *Destitution in Rural Ethiopia.* By Yared Amare. August 2003
No. 4 *Environment, Poverty and Conflict*. Tesfaye Teklu and Tesfaye Tafesse. October 2004

## Educational Materials

- Environmental Posters
- Environmental Video Films
    - **የከተማችን አካባቢ ከየት ወደየት?**
    - **ውጥንቅጥ፣ ድህነትና የአካባቢያችን መጎሳቆል**

## Africa Review of Books (Managed by FSS for CODESRIA)

- Vol. 1 No. 1. October 2004.

**Forum for Social Studies**

The Forum for Social Studies (FSS) is an independent, non-profit institution engaged in policy-oriented research on the development challenges facing Ethiopia. It provides an open forum for the discussion of public policy and promotes public awareness. FSS believes that encouraging broad participation in policy debates is an important contribution to the democratic process. To achieve its goals, FSS organizes public conferences, and publishes and distributes its research findings to policy makers and other government officials, civil society institutions, professionals, the business community, donor agencies and the public at large.

**This publication has been made possible by the FSS donor consortium which consists of the Norwegian Embassy, Netherlands Embassy, DFID, and the Irish Embassy.**